# ፈተና



ሰው የመሆን እሴህ የኅላፊት፣ በዚህ ቀጸይ [illegible]
የመኖሪያነት ፀብ ዓይም ምስጢር [illegible]
[illegible] የሕይወ ተጋድሎ [illegible]
የመቋቋም ብርታት ነሌቶ የመጣበ [illegible] አይበል [illegible]

እውነተኛ [illegible]

በPDF ያዘጋጀው...

፩ መጽሐፍ
Bookstore

የቴሌግራም ቻናል
@and_metshaf

Scanned with CamScanner

R47

# ፈተና

አስቴር ሰይፉ

ጥር - 2002

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

የመጀመሪያ እትም - ጥር 2002

## ዝምታ ነው መልሴ

"ለዋልኩት ውለታ ይሄ ነው ወይ ውርሴ?
ልፋቴ ድካሜ ይሄ ነው ወይ ውርሴ?
እንግዲህ ምን ልበል ይህ ከሆነ ቅርሴ
… ዝምታ ነው መልሴ።
"…ሾተሉ እስኪነቀል የነገር አንካሴ
የእውነት ፀሐይ ወጥታ እስከሚታይ ክሴ
እኔ አልወጣም ሸንጎ ከሳሼ ነው ዋሴ!
"…የሰው ልጅ ሆዱን ሲከፋው
ጊዜ እንደ ሰው ሲገፋው
መሄጃ መውጫ ሲጠፋው
ዝምታ ብቻ ነው ተስፋው።
"ከፀሐይ ከውጪው፣ ከንዳድ ከሃሩሩ
ዛሬ ከሰው ብሰዋል ሰውን ማስጠፉሩ
ጠላት ነው መሰለኝ ፊቴን አጥቁሮኛል
እንዲያው ያለመልኬ መልክ አሰጥቶኛል።
(ግና) "ሆድ ከታገሰ ከቻለ
የማያልፍ ቀን ምናለ?
ለክፋት ለተንኮል ምሱ
ዝምታ ብቻ ነው መልሱ።"

ከአርቲስት ማሕሙድ አሕመድ ዜማ የተወሰደ



## መታሰቢያነቱ

- ያስወላጅ ያደጋችሁ፣
- በእንጀራ እናትና አባት የተሰቃያችሁ፣
- በየጉዳናው የወደቃችሁ፣
- በባዕዳን አያያዝ የተንገላታችሁ፣
- የታፈነ ችግር ሳለባችሁ፣
- በአጠቃላይ ኃላፊነት በማይሰማቸው ወላጆች የተበደላችሁ…

እናም ለወንድምና እህቶቼ በሙሉ
እነሆ መታሰቢያችሁ!!

# ምሥጋና

- በልጅነቴ ከዋጠኝ የጥላቻ አረንቋ ውስጥ አያቶቼ መጠነኛ "ደረቅ መሬት" ሆናችሁኛል። እናንተ ባትኖሩስ? ዕጣ-ፈንታዬ በአረንቋው ጨርሶ መዋጥና መጥፋት ይሆን ነበር። ስለዚህ አያቶቼ አመሰግናችኋለሁ። ታላቅ ወንድሜም (ጋሼ ብዙነህ ተስፋ) ይሄን መጽሐፍ ለመጻፍ የበቃሁት አንተ ባስተማርከኝ ትምህርት ነውና ምሥጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

- የሥጋ ቁራጭ፣ የአጥንት ፍላጭ ሳይኖረኝ!
  ከፍት የተውኩት ቤቴ ሳይዘጋ!
  አደራ ያልኩት ቃሌ ሳይጠፋ!
  ቤት ንብረቴን ለጠበቁ "የባዕድ" ዘመዶቼ በሙሉ

- የዘመድ አዝማድ ከለላ በማይደርስበት አውላላ ባዕድ አገር ውስጥ ጥላ ሆነውኝ፣ በኑሮም እንድቋቋም የማይረሳ ታላቅ ውለታ የዋሉልኝ፡-
  - ለፕሮፌሰር አሥራት ፀጋዬ እና ለባለቤታቸው (ለታላቋ አክስቴ) መብራቴ ተስፋ (እናናዬ)
  - ለአቶ ከበደ ወልዴ እና ለልጃቸው ዘሪሁን ከበደ

- የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ከአገር እንድለቅ ባዘዘኝ ሰዓት ጠበቃ አቁሞ የተከራከረልኝ፡-
  - ለፕሮፌሰር ሚንጋ ነጋሽ

- የስደት ኑሮዬን ዓለም፣ ጎደሎ ህይወቴን ሙሉ ለማድረግ ዘወትርም የምትታትረው፡-
  - ለልጁ ሩታ አርአያ

- ለመፅሐፌ ዝግጅት አስተዋፅኦ ላደረገልኝ፡-
  - ለዶ/ር መልካም አሥራት

ሁላችሁም የከበረ ምሥጋናዬ ይድረሳችሁ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ!



# መግቢያ

ከትምህርት የሚገኝ ዕውቀት መከታ አድርጎ የሚፅፍ ደራሲ አለ። እኔ ለዚህ አልታደልኩም። ግን ኑሮ በጊዜ ሂደት ህይወቴ ውስጥ ያከማቸው አንጡራ ልምድ አለኝ። የኑሮ መራራውና ጣፋጩ ሁሉ ለእኔ ባዕዳን አይደሉም። ከፍታና ዝቅታውንም ጠንቅቂ አውቀዋለሁ። ቧጥጬ የወጣሁትን የኑሮ አቀበት በመንሸራተት ከፍታውን በአፍታ ያጣሁበት ጊዜ ብዙ ነው። አቀብ ቁልቁለቱ ጉልበቴን ተፈታትኖኝ ከግማሽ በላይ ጉዞዬን አጠናቅቂ ቀሪውን በመወጣት ላይ ያለሁ ጎልማሳ ነኝ። መጽሐፌ የዚህ ጉዞዬ አመላካች ፈለግ ናት - የትምህርት ዕውቀት ሳይሆን ልምድ ጉትጎች ሆናብኝ የከተብኳት።

የሰው ልጅ ዕድገት በቆየው ግንባታ ላይ አዲስ የመቀጠል የትውልድ ሂደት ነው። ይህ በአብዛኛው የሚታየው ታዲያ በሳይንስና በቴክኖሎጂው ዘርፍ ነው። በማኅበራዊ ህይወትና በኑሮ ልምድ ላይ የተቀጣጠለ የመረጃ መለዋወጥ ባህላችን እምብዛም የጐላ አይደለም። አብዛኛውን ጊዜ ለአዲሱ ትውልድ እንቅፋት የሚሆነው፣ አሮጌው ትውልድ ላይ ቀድሞ ደርሶበት የነበረ የህይወትና የኑሮ ሳንካ ነው። ለምን? አላፊው ትውልድ በህይወት ጉዞ ላይ ሳለ እግረ-መንገዱን መጪው ትውልድ መንገዱ እንዲቃናለት ጥርጊያውን ሊያሳምርለት ይገባል። ጉድባውን ባይደለድል እንኳን አመላካቾችን በማኖር "እዚህ ዕድሜና ኑሮ ላይ እንዲህ ያለ የህይወት ሳንካ አለ" ማለት ይገባዋል። እኔ በዚች መጽሐፍ ማከናወን የፈለግኩት ይሄንን ተግባር ነው።

ህይወቴ "የትውልድ ገበታ" ሆኖ በመማሪያነት እንዲጠቀስ ሙሉ ፈቃደኛ ስለሆንኩ እነሆ በመጽሐፍ አዘጋጅቼ አቅርቤዋለሁ። መውደቅ - መነሳቴን፣ መሳቅ - ማልቀሴን፣ መድከም - መጠንከሬን ለህሊናዬ ታማኝ በመሆን ሳላጓድል ለማቅረብ ጥሬአለሁ። እውነታን የማሟላት ጥረቴ ከወዲያ ወዲህ እያላተመ ከባቢያዊ ሁኔታዎችን ብቻ ሳይሆን የተወለዱኝንና የተወዳጁኝን ግለሰቦች እንዳነሳ ግዴታ ጥሎብኛል። አንስቼአለሁ። በዚህም አንዳንድ ሰዎች በመጽሐፌ ላይ በመነሳታቸው ቅሬታ ሊያድርባቸው እንደሚችል ከወዲሁ ይገባኛል። ይህንን ቅሬታቸውን ለማለዘብ የሚረዱ አንዳንድ እርምጃዎችን ከመውሰድ ውጭ ጨርሶ እንዳይነሱ ለማድረግ አልተቻለኝም። በመሆኑም በህይወቴ ላይ ጉልጥምት ፈጥረው ሊያጐብጡኝ የሞከሩትን ግለሰቦች ስማቸውን በመቀየር ዕይታን ከትክክለኛ ማንነታቸው



Scanned with CamScanner

ላይ ለማራቅ ሞክሬአለሁ። የኔ ፍላጐት ግለሰቦችን ማሳጣት፣ መወንጀል ወይም መውቀስ ሳይሆን በእኔ ህይወት ላይ ያጋጠሙ ስህተቶች በሌሎችም እንዳይደገሙ መከላከል ነው። መከላከል ባይቻል መቀነስ አይገድም· ብዬ ተነስቼአለሁ።

በልጅነቴ ለሌሎች ምዝበራ የተጋለጠ ህይወት ነበረኝ። "ሃይ ባይ" ባለቤት የሌለው ክምር ላይ እንደደረሰ ዝንጀሮ፣ ቤተ-ዘመዶች እንዳሻቸው ሲያመሳቅሉኝ አድጌአለሁ። በግብር ይውጣ ተዘርቼ፣ በግዴለሽነትና በጥላቻ ሥር ማቅቄአለሁ። ይሄ የጨቅላነት ሥራይ እንደ ኩፍኝ ከልጅ ልጅ እንዳይሸጋገር የዘወትር ፀሎቴ ነው። ፀሎት ብቻም አይደለም፣ የልጅነት ህይወቴን መስተማሪያ አድርጌ ከፊታችሁ አስጥቼአለሁ።

የልጅነት ዘመኔን የተካው የእልህ ህይወት ነበር። እራስን የመከላከል እልህ፣ በኑሮ ለውጥ የማምጣት እልህ፣ ለሌሎች ከለላ የመሆን እልህ፣ ደግነት ተቀብሮ እንዳይቀር የመጣር እልህ... አያድርገውና የልጅነት ህይወቴ ዕጣ-ፈንታው የሆነ ልጅ ይሄን እልሄን ቢወርስ ምኞቴ ነው። ምኞት ብቻም አይደለም፣ የእልኸኝነት ዘመንን ሳልሸፋፍን እጃችሁ እንዲገባ አድርጌአለሁ።

በተረፈ "አልወለድም!" ከሚል ልቦለዳዊ ፅንስ ይልቅ ወላጆች "አልወልድም!" ማለት ይቻላቸዋል ብዬ አምናለሁ። ለመውለድ ከወሰኑም በቅድሚያ ወደዚህ ዓለም ስለሚያመጡት ህፃን የተመቻቸ ህይወት በፅኑ እንዲያስቡ በእኔ ህይወት እመክራለሁ። ህይወቴን በሴጣው ማቅረቤ ከምክር አንድ እንደሆነ አምናለሁና።

መልካም ንባብ!<br>
አስቴር ሰይፈ<br>
ጥር - 2002





# ክፍል አንድ
# እቴቴ

## - 1 -

በጋ ሲሆን...

...የቤታችን በረንዳ ነግቶ እስኪመሽ ለፀሐይ ብርሃን የተጋለጠ ነው። በማለዳ የየረር ተራራን ታክካ ስገግ እያለች የምትወጣው ለጋ ጀንበር እየጋመችና እየጋለች ወደ ምዕራብ ታዘቀዝቃለች። የወጨጫ ተራራ ሹል አፉን አሞጥሙጦ እንደ ቅልጥም መቅኔ ብርሃኗን እያዝለገለገ ይሰለቅጣታል። አቤት ያኔ፣ እንዴት ሆዴ ይባባል! ከሰማዩ ጋር ውስጤ ይጨልማል። ግን ሁልጊዜም በጋ አይሆንም - ክረምት ይገባል።

እንደዛሬው ክረምት ሲሆን...

...ከመሬት ጋር ነፍሴ ይጨቀያል። ለሰማይ በደል የተጋለጠችው ምድር መሸሸጊያ እንደምታጣ እንዲሁ ጥጋት ይጠፋኛል። የእማዬ አሻሮ መቁያ ብረት ምጣድ የተደፋብኝ ያህል ሰማይ የፀጉሬን ጫፍ ነክቶ ይንጠለጠላል። በቀን ጭልም ይላል። ያቺ የብርሃን እናት፣ ያቺ ብርሃን አግታ ጨረር የምትታለበው ጀንበር የት ነች? ያቺ የወጨጫን ተራራ እንደ ጥጃዋ ቁልቁል እያየች ለመላስ የምታሰግገው ጀንበር የት ነች? ሆዴ ይባባል። ቤተሰቦቼን ይመስል ፍቅር የማትሰስተኝ፣ አድልኦ የማትፈፅምብኝ ጀንበር እሷም ሰለቸችኝ?

የኃይለ-መለኮት መንገድ ጭር ብሏል። አልፎ አልፎ ጭንቅላታቸውን ትከሻቸው ውስጥ ቀብረው የሚንቶሰቶሱ ሰዎች ያልፋሉ። እንደ ሠይፍ አግድሞሽ ለሚወነጨፈው ዝናብ እናታቸውን ጋርጠውና በግንባራቸው አስታከው እያዩ ይሄዳሉ። ወጨፎው በረንዳችን ድረስ ዘልቆ እግሮቼን እያራሰ ነበር። ጫማ የማያውቁት እግሮቼ ለማብረቅረቅ የሚሞክሩት ይሄኔ በመሆኑ ዝም ብዬ እያቸዋለሁ። ከውሃ ሲወጡ ወዲያው አመድ ይወርሳቸዋል።

መላልሶ ይባርቃል። ሰማዩ ሲተረተር እደነግጣለሁ። ተመሳሳይ መብረቅ ከወደቤት ውስጥ ይሰማኛል። ከኔ በስተቀር ሁሉም ተሰባስበው የሚባርቅ ሳቅ ያሰማሉ። ለእነሱ ሳቅ እኔ እባትታለሁ። እንደ ወጨፎው እግሬ ላይ አትኩረው፣ እንደ ጀንበሯ በግድግዳ ተጀቡነው እንደ መብረቁ ይባርቃሉ። እኔስ?



Scanned with CamScanner

እኔም አብሬያቸው ነበርኩ። በኋላ ላይ እንደሰማሁት ሰውየው የጃንሆይ አንጋች ነበሩ።

ቤታቸው ስንገባ ዓይናቸው አያይም። ደግሞም ሰው ሁሉ ሰላምታ የሚያቀርብላቸው በርከክ ብሎ እግራቸውን በመሳም ነው። ሁሉም ተራ በተራ እየሄዱ እግራቸውን ስመው ሲመለሱ የእኔም ተራ ደርሶ እግራቸውን ልስም አጐነበስኩ። ለምን እንደሆነ እንጃ፤ የሰው እግር መሳም አልወድም፤ ይቀፈኛል። በዚህም የምስም መስዬ እግራቸው ላይ እጄን አስቀመጥኩና የእጄን ጀርባ ልስም ሳጐነብስ ሰውየው፤

"አንቺስ ማነሽ?" አሉኝ ፀጉሬን እየነካኩ፤ በዚያ አስፈሪ ወፍራም ጐርናና ድምጻቸው።

በጣም ትልቅ ሰው ስለሆኑ ምናልባት ፈርቼ ወይም ዓይን የሌለው ሰው ላይ የመጀመሪያዬ ስለሆነ ያ ነገር ቀልቤን ሰርቆት ይሁን አላውቅም እንዳጐነበስኩ ዝም ብዬ ስቀር ሌሎቹ "እህታችን ናት" ሲሉ በእኔ ፋንታ መልስ ሰጡ።

"እ… በፀጉሯ አወቅኋት። ያቺ ዲቃላዋ አይደለች" አሉ እኒያ ትልቁ ሰውዬ።

ዲቃላ? ይሄን ቃል ዛሬም ለሁለተኛ ጊዜ መስማቴ ነው። ምን ማለት ይሆን?… ፀጉሬስ እንደ ሌሎች እህቶቼ ረዥምና ለስላሳ ያልሆነው ለምን ይሆን? ለምን የኔ ብቻ አጭርና ከርዳዳ ሆነ?

ወዲያውኑ በሰፌድ የተቀመጠ ብርቱካን መታደል ጀመረ። ለሁሉም ተሰጥቶ እኔ ጋ ሲደርስ ቆመ። ከዚያ ከሌላ ሰፌድ ላይ የተቀመጠ ብርቱካን ሊሰጡኝ ሲሉ እልህ ይዞኝ በንዴት "አልፈልግም" አልኩ።

የዛን ቀን ለሌሎቹ ከተሰጣቸው ሰፌድ ላይ ያልተሰጠኝ ዲቃላ በመሆኔ ነው ስል ደመደምኩ። እናም ሳይደብቅ ትክክለኛ ትርጉሙ እንደሚነግረኝ በሙተማመን ጋሼን ጠየቅኩት። እሱም "ማነው እንዲህ ያለሽ?" ብሎ ከመቆጣትና አለማሽን ከመገረፍ ያለፈ የቃሉን ትርጉም ሊነግረኝ አልፈቀደም።

አ! ሁሉም በአለማሽ ላይ እጃቸውን እንዲሰነዝሩ የሚያደርግ ከሆነ፤ ይህ ቃል እውነትም ክፉ ቃል መሆን አለበት!

የማወቅ ጉጉቴ ጨምሮ ትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ ተቀምጬ አስተማሪው እስኪመጡ በመቁነጥነጥ እየጠበቅሁ ነው። ተመሳሳይ ኮትና ሱሪ የለበሱት አስተማሪያችን ሲገቡ ሁላችንም እኩል ከተቀመጥንበት ብድግ አልን።

"ጉድ ሞርኒንግ ስቱደንትስ"
"ጉድ ሞርኒንግ ቲቸር"
"ሲት ዳውን ስቱደንትስ"
"ታንኪዩ ቲቸር"





ሁሉም ሲቀመጥ እኔ ብቻ አንድ እጄን ወደላይ አንከርፍፌ እንደቆምኩ ቀረሁ። የክፍሉ ልጆች አጉረመረሙ። ከጐኔ የተቀመጠችው ፈሪ ጓደኛዬ ቀሚሴን ወደታች ትጐትተው ጀመር።

"ምነው አስቴር? ሽንት ቤት መሄድ ፈለግሽ?" መምህሩ ጠየቁኝ።

"አይደለም፤ ጋሼ። አንድ ጥያቄ አለኝ"

"መልካም ጠይቂኝ" አሉ ፊታቸው ላይ መገረም እየተነበበ።

"ዲቃላ ምን ማለት ነው?"

ዘለግ ላለ ጊዜ በዝምታ አተኩሩብኝ። ደነገጡ ለበል? ወይስ እንደኔ ትርጉሙን አያውቁትም? በሃሳብ ነጉደው ወለል ወለሉን እያዩ ዝም ሲሉኝ ጊዜ፤ ጥያቄዬን ቀለል አድርጌ ለማቅረብ ፈልጌ ነው መሰል፤ "ጫማ የሌለው ልጅ ማለት ነው እንዴ?" አልኩ።

ከብዙዎቻችን በዕድሜ ከፍ ያሉ ጥቂት ተማሪዎች ሳቃቸው አመለጣቸው። የተቀሩትም ተከተሏቸው። ግን አስተማሪያችን ከቅድሙ ይበልጥ ኮስተርተር ሲሉባቸው ወዲያውኑ ሁሉም ዝም፤ ጭጭ አሉ።

እኔም ክፍሉ ውስጥ ያረበበው ፍርሃት ተጋብቶብኝ ምነው ባልጠየቅኩ፤ በቀረብኝ እያልኩ መፀፀት ስጀምር፤

"ማን ሲል ሰምተሽ ነው?" አሉ አስተማሪያችን።

"አለማሽ"

"አለማሽ ምንሽ ናት?"

"እህቴ - ታላቅ እህቴ።"

"ከማን ጋር ነው የምትኖሪው?"

ከአባቴ፤ ከእናቴና ከወንድም እህቶቼ ጋር እንደምኖር ነገርኳቸው።

"በይ፤ ዲቃላ ማለት ቆንጆ ልጅ ማለት ነው፤ እሺ" አሉኝ።

ሙሉ ለሙሉ ባላምናቸውም ደስ አለኝ። እማዬና ጋሼ ግን የኔ ቆንጆ ልጅ መባል ለምን ያናድዳቸዋል? - ያውም አለማሽን እስከመገረፍ የሚያደርስ ንዴት!… አለማሽስ ብትሆን እንዴት ቆንጆ ልጅ ልትለኝ ቻለች? አሃ… አላለችኝም ለካ! እማዬም እቴቴም የማይወዱሽ ቆንጆ ልጅ ስለሆንሽ ነው ነበር ያለችው በተዘዋዋሪ።

"ለማንኛውም ነገ ወላጅ ይዘሽ ነይ" አሉኝ አስተማሪያችን።

የዚያኑ ዕለት "ወላጅ ይዘሽ ነይ" መባሌን ለጋሼ ስነግረው፤ "ምን አጥፍተሽ ነው?" የሚል ጥያቄ አስከተለብኝ - በጩኸት።

"ም….ን….ም" አልኩት፤ ዘሎ ይማታል ብዬ እየተሸማቀቅኩ።

"የሆነ ያጠፋሽውማ ነገር አለ። እውነቱን ንገሪኝ! ምን አጥፍተሽ ነው?!"

መላ ሰውነቴ በፍርሃቴ እየተርገፈገፈ "እረኔ ምንም አላጠፋሁም!" አልኩ። ላለሳልሰው እየሞከርኩ ሳለ ድንገት ከተቀመጠበት ብድግ አለ። በቃ አለቀልኝ። ያ አስቃቂ ዱላ ዛሬም ላይቀርልኝ ነው? ከመመታቴ በፊት ተንፋረቅኩ። "ጋሼ! ቆይ እንዳትማታ… መጀመሪያ አስተማሪያችንን ጠይቅ!"



Scanned with CamScanner

የዚህ ዓለም ግንዛቤ ዋስትናው ምንድነው? ለአንድ ትንሽ ልጅ ከቤተሰቦቿ ውጭ ምን እውነታ አለ? አንድ እውነታው ወደ ሐሰት ሲለወጥ ካየ ሌላው ሁሉ ትርፍ አይደለምን?

ትርፍራፊ ሳቅና ጨዋታ የሚቃርመው የልጅነቴ ደመ-ነፍስ ደነገጠ። መሳቅ፣ መጫወት ቀነስኩ። መተከዝ፣ ለብቻ አንድ ቦታ ኩርምት ብሎ መቀመጥና ፈዝዞ መዋል መለያ ባህሪዬ እየሆነ መጣ። አዕምሮዬ ሁሉ ወደ እናቴ ብቻ ኮበለለብኝ። ጭንቅላቴ አንድ ነገር ብቻ በማሰብ ተጠመደ። ለምን ክፉ ሆነችብኝ? ለምን ይህን ያህል ጨከነችብኝ? ልጆቿ ምርጥ ምርጥ ልብሶች ሲለብሱና ምርጥ ምርጥ ጫማዎች ሲጫሙ እኔ በባዶ እግሬ እንድኳትን ለምን ፈረደችብኝ?

ለነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች በቂ መልስ አጥቼ እንደተምታታብኝ ትክዝ ብዬ መሬት እጭራለሁ። ሳወጣ ሳወርድ እውላለሁ፤ ወደኋላ እየተመለስኩ ብዙ ውል የሌለው ነገር ሳውጠነጥን አድራለሁ። እንደዚያም ሆኖ እናቴ እኔን የጠላችበት፣ በእኔ ላይ የጨከነችበት ምክንያት ሊገለጽልኝ አልቻለም።

ዛሬም ምንም የተለወጠ ነገር የለም። በርግጥ እሷ የእውነት ወልዳኛለች? ብዬ እንድጠይቅ የሚያደርጉኝን በርካታ የግፍ ግፎችን እየፈፀመችብኝ ነው። ዛሬም ብታመም፣ ብድን ዞር ብላ አታየኝም።

አሁን ዘጠኝ ዓመት ሆኖኛል። መነሻው ባልታወቀ ምክንያት መላ ሰውነቴ፣ ጭንቅላቴ ሳይቀር በቁስል ተመትቷል፤ ትንሿን የእጅ ጣት ማሳረፍ የሚችል ከቁስል ነፃ የሆነ ሰውነት የለኝም። ከቁስሌ ጋር ተጣብቆ የሚውለውን ልብሴን ማታ፣ ማታ ሳወልቅ ነፍሴ ተመንጥቃ ልትወጣ ትደርሳለች።

እንዲህ ቁስልስል ብዬ በዝንቦች ተወርሬ በረንዳ ላይ ቁጭ ብዬ እውላለሁ። እያንዳንዱ ንቅናቄ የጥዝጣዜ ዋጋ ስለሚያስከፍለኝ ግድ ካልሆነብኝ አንገቴን እንኳን ዞር አላደርግም። ዝንቦቹንም ለማባረር አልሞክርም። እንደዚህ የተፋፋቅሁ ሐውልት መስዬ እንደተቀመጥኩ ጋሼ ሰቦቃ መጣ። ዕድሜውን የገፋው የአያቶቼ ጋሪ ነጂ ሆኖ ነው። የግዙፍ ሰውነቱ ጥላ እንጂ እሱ ከብዶኝ አያውቅም። አሁንም ስግደድ ብሎ እንደቆመ ያየኛል። የአንገቴንና የማጅራቴን ቁስል ትዩ ቀና ብዬ ለማየት ሞከርኩ። ሰከሯል። ከዚህ ጋር እያዘነልኝ እንደሆን ከፊቱ ላይ አነበብኩ። ከሰከረ ለማንም ደንታ የለውም። የመሰለውን ይናገራል። በዚህ የተነሳ አባዬ ከቤት እንደሚያባርረው ብዙ ጊዜ ዝቶበታል።

ይሄኔ እንጀራ አባቴና ወላጅ እናቴ ሁሌ እንደሚያደርጉት አያቴ በር ላይ መኪናቸውን አቁመው ወረዱ። ጋሼ ሰቦቃ አንዳች ነገር ለማድረግ ያሰበ ይመስል የቆመበት እየተናጠ ይመለከታቸዋል። ዝንጥ ብላ ሽቶ ተርከፍክፋ በኩራት የምትራመደው እቴቴ ላይ ሙሉ ትኩረቱን አድርጎ መናገር ጀመረ።





"ልጅሽ እንዲህ ቆሳስላ፣ በዝንቦች ተወርራ ስትሰቃይ ትውላለች፤ አንቺ ደግሞ ቂቅ ብለሽ ለብሰሽ እንደ ልዕለት አምረሽ የትም ስትዞሪ ትውያለሽ"

ሁለቱም ቁብ ሳይሰጡት አልፈውት ሄዱ።

* * *

ሲያሳክከኝ የቆየው የሰውነቴ ክፍል ህመም ዕረፍት ነስቶኛል። እዛችው ቦታ ላይ በዝንቦች ተቀብሬ ቁጭ ባልኩበት ሰዓት የአያቴ የአክስት ልጅ ኮሎኔል መለሰ ተካ ከጋሼ ተሻለ ጋር በመሆን እናቴን ለመጠየቅ የኛን በር አቋርጠው ሲያልፉ ያዩኝና ደንገጥ ብለው፣

"ኡ-ንዴ?! እቺ የብርክት ልጅ አይደለችም?..... ምነው ምነው ተሻለ? መቅደስ ብትሆን፣ እንዲህ ዓይንህ እያየ ዝም ትላት ነበር? ለምን አታሳክማትም?" ሲሉት

"አላስመዘገብኳትማ!" አላቸው ትክሻውን በምንቸገረኝነት እየናጠ። ያኔ ማስመዝገብ ምን እንደሆነ አላውቅም።

"እይ፣ ትክክል አይደላችሁም! እግዜር የማይወደው ሥራ ነው የምትሰሩት!" እያሉ ኮሎኔሉ እንጀራ አባቴን ሲወቅሱ፣ ወላጅ እናቴ ከቤት ብቅ ብላ ተቀላቀለቻቸው።

"ብርክት፣ እያት እስኪ ይቺን ልጅ! እንደዚህ እስክትሆን ድረስ እንዴት ዝም ብላችሁ ታዩዋታላችሁ?"

"በቃ፣ ዕድሏ ነው። ምን ይደረግ?" አለች እናቴ እሷም እንደ ባለቤቷ ትከሻዋን እየሰበቀች።

"ለሌሎች ልጆቻችሁስ አትፈሩም? የሚጋባ በሽታ'ኮ ሊሆን ይችላል። ቢያንስ የቁስሉን ምንነትና መንስኤው እንኳ ጠይቃችሁ ብታውቁ ምናለ?"

"ይልቅ ግባ፣ በዚህ ጠራራ ፀሐይ እደጅ አትቁም!" አለች እናቴ፣ በነዚያ አስፈሪ ዓይኖቿ ገላምጣኝ ስታበቃ።

"እውነት የምትሰሩት ሥራ በጣም የሚያሳዝን ነው.....በል አሁን ለግዛው (ለሾፌሩ) ንገርና ቶሎ ወደ ህክምና ይዟት ይሂድ" አሉት ኮሎኔል በለጠ፣ እንጀራ አባቴን።

እስከዚያች ቀን ድረስ ከአውቶቡስ ውጪ የቤት መኪና ላይ ተሳፍሬ አላውቅም ነበር።

የክብር ዘበኛ ሆስፒታል ዶክተር እንዳየኝ በድንጋጤ ዓይኖቹ ፈጠጡ። "እስካሁን ለምን ሳታሳክሟት ቆያችሁ? አባት፣ እናት፣ ዘመድ ጉረቤት የላትም?" ብሎ በንዴት ሾፌሩ ላይ ጮኸ። በጥልቅ ሀዘን ጭንቅላቱን በኃይል ሲወዘውዝ፣ የጉዳቴ መጠን አሁን የተገለጸልኝ ይመስል ድንገት ለቅሶዬን አስነካሁት። ሆስፒታሉን በጩኸቴ አናወጥኩት። ማን አባብሎ ዝም ያሰኘኝ!? በዚያ ሰሞን አዲስ የተቀጠረች የእናቴ ሠራተኛ



Scanned with CamScanner

እንዲህ ቆሳስዬ ውሃ ስቀዳ አይታኝ "ምን ዓይነት ጨካኝ እናት ናት! ምን ዓይነት ቤተሰብ ናቸው እነዚህ?" ብላ ስትናገር የሰማኋት ጊዜ እንኳ እንደዚህ አላለቀስኩም፡፡

ሀኪሙ በመከራ አባብሎ ዝም ካሰኘኝ በኋላ አክሞ፣ በየቀኑ እየተመላለስኩ መርፌ እንድወጋ አሳስቦ ሸኘኝ፡፡ ብዙ መርፌ እንደተወጋሁ ነበር ቁስሉ ጠገግ ያለልኝ፡፡

አዎን፣ ታሪኬን በማወቁ ምንም የተቀየረ ነገር የለም፡፡ ዛሬም ሳላጠፋ እመታለሁ፡፡ እንዲያውም ነገሩ የከፋ ደረጃ ደርሶ ደግ ስሰራ ሁሉ መመታት ጀምሬያለሁ፡፡ ከነዚህ መሃል የእናቴን ልጅ ቢንያምን ከመኪና አደጋ ያዳንኩበትን ሁኔታ ልጥቀስ፡፡ በወቅቱ ጋሼ ተሻለ የመንግስት ቦልስዋገን መኪና ይነዳ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን እኔና መቅደስ ከበር ውጪ እየተጫወትን ነው፡፡ ቢንያም ደግሞ ከእኛ ፈንጠር ብሎ ከአባቱ መኪና ኋላ በሆነ ነገር ብቻውን ይጫወታል፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ኮ/ል ተሻለ እየተጣደፈ ከቤት ይወጣና መኪናውን አስነስቶ የቢንያምን ከመኪናዋ ኋላ መኖር ልብ ሳይል የኋላ ማርሽ አስገብቶ መኪናዋን ማንቀሳቀስ ጀመረ፣ ይኸኔ በድንጋጤ "ወጣበት! ወጣበት! እእእ!" ብዬ እየጮህኩ የዕውር ድንብሬን መሮጥ ጀመርኩ፡፡ ለካ ከተቀመጥኩበት ተስፈንጥሬ ስነሳ መቅደስም እንደኔ ልሩጥ ስትል ቀሚሷን ረግጬባት ኖሮ በአፍ ጢሟ ትደፋለች፡፡ ምላሷ ጥርሷ ውስጥ በመወተፉም ትደማለች፡፡ የዛን ቀን ቢንያምን ባዳንኩት፣ መቅደስ ወድቃ ደማች ተብሎ የወረደብኝን ዱላ አሁን ሳስታውሰው እንኳ ያመኛል፡፡

አዎን፣ ድብቅ ታሪኬን በማወቁ የተለወጠ ነገር የለም - አሁንም እውነት እውነቱን ብናገርም ማንም አያምነኝም፡፡ አለማሽ የተናገረችው ሁሉ ግን እውነት ነው፡፡ ለምሳሌ አለማሽ አንድ ቀን ማታ ላይ ፍራንክ ትሰጠኝና "እነ መብራቴ ፓስቲ ግዥልን ብለውሻል" ትለኛለች፡፡ ጨለማ እንደምትፈራ ስለማውቅ እሺ ብያት ገዝቼ ወደ ቤት እየተመለስኩ ሳለ አባዬ መንገድ ላይ ያገኙኛል፡፡ "ከየት ነው የምትመጪው?"

"እነ እናናዬ ፓስቲ ግዥ ብለውኝ"

ዝም ዝም እንደተባባልን ቤት ገባን፡፡

"በዚህ ጨለማ ለምን ላካችኋት?" አባዬ ተቆጣቸው፡፡ እነሱ "እረ እኛ አልላክናትም!" ብለው ሽምጥጥ አድርገው ካዱ፡፡ አባዬ በቀጥታ ቃላቸውን አምኖ "ፍራንኩን ከየት አመጣሽ?" እያለ በኃይል ገረፈኝ፡፡ እኔ እነሱ ፍራንኩን ከየት እንደሚያመጡት አላውቅም እኮ! ሰርቀውት ይሆናል ብዬ እንዳላስብ በዚያን ሰዓት ፍራንክ መስረቅ ብሎ ነገር በዚህ ዓለም ስለመኖሩ እንኳ የማውቀው ነገር የለም፡፡ "ሁሌ ነው የሚልኩኝ፣ እኔም ሁሌ ነው የምገዛላቸው" ብዬ እውነቱን ብናገር፣ ብጮህ አባዬ እንዴት ይመኑኝ?!





በዚያ ላይ ፓስቲው እዚያ ለነበረ ሰው ሁሉ ተከፋፍሎ ሲሰጥ፣ ከመሃላቸው አንድ ስንኳን "ልጅ ናትና ትጓጓለች" ብሎ ሊሰጠኝ የሞከረ አልነበረም፡፡ ተገርፌም፣ ተቁለጭልጬም ምንም ሳላገኝ ቀረሁ፡፡ ያለኝ አማራጭ በፓስቲው ምትክ እንባዬን መዋጥና ተጠቅልሎ መተኛት ሆነ፡፡

* * *

እንደ ልማዴ በዙሪያዬ ያሉ ሰዎች እኔ ላይ የሚያሳርፉት የክፋት በትር ሆድ አስብሶኝ እያለቀስኩ ነው፡፡ ብቻዬን ተቀምጬ መሬት እየጫርኩ በምብሰለሰልበት በዚያ ቀን እማዬ ከየት መጣች ሳይባል "መሬት አትጫሪ! ተነሺና ተጫወቺ!" ብላ መታችኝ፡፡ መሬት መጫር ደግሞ ያስመታል እንዴ? ገረመኝ፣ ከፋኝ፡፡ "መሬት አትጫሪ" ማለት ያለዕድሜሽ ትካዜና ሃሳብ አታብዢ ማለት መሆኑ የገባኝ ትንሽ ዕድሜ ከጨመርኩ በኋላ ነው፡፡

በጊዜው ግን መጠላቴ አንገብግቦኝ ለሰዓታት ስቅስቅ ብዬ አልቅሻለሁ፡፡ ይኸኔ ነበር እኒያ የወላጅ አባቴንና እናቴን ማንነት የጠቆሙኝ ሴትዮ ኩርምት ብዬ እተቀመጥኩበት ድረስ መጥተው፣ "ሁሌ እንዲህ ስትንሰቀሰቂ ከምትኖሪ ለምን አባትሽ ጋ አትሄጂም?" ያሉኝ፡፡

"እንዴት እንደሚኬድ አላውቅም" አልኳቸው እየተነፋረቅኩ፡፡

"እንዴት እንደምትሄጂ እኔ እነግርሻለሁ፣ በደንብ አድምጪኝ፡፡ ለአውቶቢስ መሳፈሪያ የሚሆን ገንዘብ እኔ እሰጥሻለሁ፡፡ አንቺ መጀመሪያ ቀጥታ ወደ ቀጨኔ መድኃኔዓለም ትሄጂና ከዚያ ወደ ሩፋኤል የሚያስወጣው መንገድ የቱ ነው? ብለሽ ትጠይቂያለሽ፡፡ ከዚያ አንድ ቁጥር ማዞሪያ ጋ እንደደረስሽ... ወርቅ ጥርስ ያለው፣ ጥቁር ማርቼዲስ መኪና የሚነዳው፣ ጠንቋዩ ሰውዬ ብትይ ማንም ያሳይሻል"

ያሉኝን ነገር እንዳይጠፋብኝ ስደጋግም፣ ስደጋግም አደርኩና በማግስቱ ቃል የገቡልኝን የመሳፈሪያ ፍራንክ ልቀበል እሳቸው ዘንድ ሄድኩ፡፡ አራት ብር እንደሰጡኝ ወዲያውኑ ለማንም ሳልናገር በጠቆሙኝ መሠረት በቀጨኔ ጫካ አቋርጬ፣ ወደሩፋኤል የሚያስገባ መንገድ ይዤ፣ አንድ ቁጥር ማዞሪያ ስደርስ ወርቅ ጥርስ ያለው፣ ጥቁር መኪና የሚነዳውን ጠንቋዩን ሰውዬ ብዬ እያጠያየቅኩ ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ አባቴ ቤት ደረስኩ፡፡ በወቅቱ ይዘንብ ስለነበር ልብሴ በስብሶ ገላዬ ላይ ተጣብቆ ነበር፡፡

የግቢውን በር አንኳኩቼ ስገባ በረንዳው ላይ አባቴ ቁጭ ብሎ በመቀስ የበግ ፀጉር ሲቆርጥ አየሁት፡፡ አንዲት የጥቁር ቆንጆ አጭር ሴትም ከጐኑ ቆማለች፡፡

አባቴ ልክ እንዳየኝ ደንገጥ ብሎ መቀሱን ቁጭ አደረገና፣ "እንዴት ብለሽ መጣሽ? ማን አመጣሽ?" ሲል ጠየቀኝ፡፡



Scanned with CamScanner

መስላችሁ የሙቀት መጠናችሁን ለማረጋገጥ ግንባራችሁ ላይ ያረፈ የእናት እጅ አጣጥማችሁ ታውቃላችሁ? የመንገድ ዳር ቆሻሻ አልጋ ላይ የሚወጣው መቼ ነው? እኔ ይሄን ክብር ለማግኘት ከመንገድ ዳር ያነሰ ተስፋ ነበረኝ። ግን ሆነ።

እናቴ በረጅሙ የህይወት ጉዞ እንዳልደከም፣ ተስፋ እንዳልቆርጥ ጥቂት የፍቅር ስንቅ ልትቋጥልኝ ያሰበች ይመስል ነበር። ከዳንኩ በኋላ የድሮው ሁኔታዋ ሥፍራውን ሲይዝ ይታወቀኝ ነበር። አንዳንዴ "ምናለ እዚያው እጇ ላይ ቅርት ባልኩ" እላለሁ። የእናቴ እንደ ድሮ መሆን የአካባቢውን ሁኔታ ወደነበረበት መልሶታል።

የዚያኔ ምን አጋጥሞኝ ለህመም እንደተዳረግኩ ነገርኳቸውና ሁለተኛ ምንም ዓይነት ስርቆት እንደማልፈፅም ለራሴም ለእነ እማዬም ቃል ገባሁላቸው። የአባዬን ካፖርት ለጓደኞቹ በሦስት ብር መሸጤን መናዘዝ መሰደቢያና መጨቅጨቂያ ሆኖኛል። መልሼ ተመሳሳይ ጥፋት ላለመድገም ቃል ከገባሁ በኋላም ባላደረግሁት ነገር መከሰስ አልቀረልኝም።

"ይህች ልጅ እኮ አሁንም አልታረመችም" ሲሉኝ እሰማለሁ።

"ምንድነው?" ስል፣

"ከእናትሽ ቤት አስር ብር ሰርቀሻል" ይሉኛል። ሃያ አምስት ሳንቲም ሰርቄ እማዬ በበርበሬ ያጠነችኝ ዕለት እንኳን እንዲህ አልተንገበገብኩም። ከእናቴ ቤት አስር ብር ላነሳ ቀርቶ፤ እነሱው ራሳቸው ሲፈትኑኝ ፊት ለፊት የሚያስቀምጡትን ሳንቲምም አላነሳሁባቸውም።

እንዲህ ባሉኝ ሰሞን እናቴ ወልዳ ወተት የማመላልስላት እኔ ነበርኩ። ያን ቀን ግን ባጋጣሚ ወተት ይገፍ ስሄድ ጋሼን በር ላይ አግኝቼው ወተቱን ለሠራተኛዋ ሰጥቻት ከበር ነበር የተመለስኩት። ደግሞም ጋሼ ራሱ ነው ከበር መልሶ ወደቤት ይዞኝ የመጣው። "ጋሼ ከመምጣቱ በፊት እውጪ ይገርፍሻል" ተባልኩ።

ካደረግሁ አደረግሁ ነው የምለው። ፍርጥም ብዬ "የማውቀው ነገር የለም" አልኩ።

"ካንቺ በስተቀር እዚያ ቤት የገባ ሰው የለም" አሉኝ። በእውነቱ ያለሥራዬ ስም ሰጥተው ሲወነጅሉኝ መፈጠሬን ጠላሁ። አንድ ክፍል ውስጥ ገብቼ "ጋሼ ሳይመጣ እኔም አልወጣም" አልኩኝ። ቆየት ብዬ እዚያ ቤት ጨርሶ አለመግባቴን አስታወስኩ። ይህንኑ ስነግራቸው እንደልማዳቸው አልሰሙኝም።

የዚያን ዕለት ባጋጣሚ ጋሼ ቤት ሳያድር ቀረ። መምጫው ሰዓት እንደረዘመብኝ አድሬ ዋልኩና፣ በነጋታው እሱ ሲመጣ እውነቱን ነግሯቸው ነፃ አወጣኝ።





# ክፍል ሦስት

# የፅናት ጎህ

## - 1 -

አሁን ወደመጉርመሱ ደርሼያለሁ። የአስራ አራት ዓመት ልጅ ሆኛለሁ። በእነዚህ አስራ አራት ዓመታት የሌለኝ፣ የጐደኝ ነገር ይበዛል። ሕይወቴ በሸንቁሮች የተሞላ ነው። እንደ ልጅነቴ ኃላፊነታቸውን የሚወጡልኝ ወላጆች የሉኝምና ለእኔ የተተወው ችግር ብዙ ነው። እናትና አባት የለኝም ማለቱ ይቀላል፤ የእነሱ አለመኖር ደግሞ ብዙ ብዙ ነገር አጉድሎብኛል። እስቦ የሚያለብሰኝ የለኝም፤ ጫማ አጥቼ ባዶ እግሬን ስኳትን የሚያዝንልኝ የለም። እናቴን ጨምሮ ሁሉም ቤተሰቤ ባዶ እግሬን መሆኔ ዕጣ ፈንታዬ እንደሆነ የሚቆጥሩ ይመስለኛል።

መኝታ እንኳ የለኝም። ከአለማሽ ጋር እተኛ በነበረ ሰዓት በአንሶላውም በብርድ ልብሱም ስለማንስማማ እጣውላው ወለል ላይ ተኝቼ የማድርበት ጊዜ ይበዛ ነበር። እዚያው ደረቅ ጣውላ ላይ ያለአንሶላና ያለብርድ ልብስ ተኝቼ ሳድር፣ እናቴ ባኗ ከአስመራ ካመጣቸው ትርፍ ብርድ ልብሶች አንዱን እንኳን ልትሰጠኝ ፈቃደኛ ሆና አልተገኘችም - ያውም ባኗ ስጪያት ብሎ ለምኗት ነበር። እሷ ግን ወይ ፍንክች! ሌላው ቀርቶ የቀየረችውን አሮጌ ልብስ ለእኔ ከመስጠት ይልቅ እንደ አልባሌ ነገር ጠቅልላ ዕቃ ቤት ውስጥ መወሸቅን ትመርጣለች።

ይህ ዓይነቱ ተደጋጋሚ ግፍ፣ ጭካኔና ክፋት አልለመድ ብሎ ሁሌ እንዳዲስ ቢያንገበግበኝም፣ አሁን አሁን መቻልን እየተማርኩ መጥቼያለሁ። እውነትም አድጌያለሁ! እውነትም ልብ ገዝቻለሁ! ምክንያቱም ለምን አላደረጉልኝም ብዬ እጃቸውን ከመጠበቅ ይልቅ በምችለው ሁሉ ሕይወትን መጋፈጥ እንዳለብኝ እየተሰማኝ መጥቷልና። በዚህም ከመንገድ የማነሳውን የሽራ ጫማና የሲሊፐር ሶል ተጠቅሜ ለራሴ ጫማ መስራትን ለመድኩ። ከመርካቶ የተቆራረጡ ጨርቆችን ለቃቅሜ አምጥቼ በጆንያ ለራሴ ፍራሽ መስራትን ተማርኩ። ከላይ ሥጋጃውን እንደ ብርድ ልብስ መጠቀምም ቻልኩ።

❋ ❋ ❋



Scanned with CamScanner

ሌላ ማንም ወገን ዘመድ የለሽም" እያለ በሥራ እንድትጋ ይገፋፋኝ ያዘ:: እኔም የውስጥ ግፊቴን አዳመጥኩ:: ‹አዎን፣ መስራት አለብኝ› አልኩ፤ ለሥራም ታጥቄ ተነሳሁ::

ግን ምን ልስራ? ራሴን ጠየቅሁ:: በዐገር ሥራ ባጠራቀምኩት ጥቂት ብር መነሻነት ምን ልሰራ እችላለሁ? የሆነ የረባ ሃሳብ ጣል እንዲያደርግልኝ ትንሹን አዕምሮዬን አስጨነቅኩት::

ጊዜው አብዮቱ ፈንድቶ ረብሻው መረጋጋት የጀመረበት ጊዜ ነው:: በወቅቱ ትልቋ አክስቴ፣ መብራቴ፣ ዕድገት በህብረት ዘመቻ ልትሄድ ዳቦ ቆሎና ቆሎ እየተዘጋጀላት ነበር:: አሃ... በድንገት ምን ልስራ? ለሚለው ጥያቄ መልሱን እዚያው ውስጥ አገኘሁት::

አላመነታሁም:: ወዲያውኑ ባለኝ ብር ዳቦ ቆሎ፣ ቆሎና በሹካ ቅርፅ ወጥቶለት የሚጠበሰውን "ክልክል" የሚባል ብስኩት አዘጋጀሁና ትምህርት ቤት አካባቢ እየሄድኩ ንግዴን ‹ሀ› አልኩ:: ፈጣን ውጤትም አገኘሁበት:: በዚህ የተነሳ የፋብሪካ ምርት የሆነውን ብስኩት ከሱቅ እሽጉን በመግዛት ነጣጥዬ በችርቻሮ መሸጥ ጀመርኩ:: ከትምህርት ቤት ሰዓት ውጪም በየቦታው እየዞርኩ ለተጠቃሚዎች በማቅረብ ንግዴን አጧጧፍኩት::

ሳንቲሙ ጠርቀምቀም ሲልልኝ የመስራት ብርታቴም የዚያኑ ያህል ጨመረና ከዚያ ጉን ለጉን የተለያዩ ዓይነት ክሮችንና ለሹራብ ስራ የሚያገለግሉ ዕቃዎችን በመግዛት ሹራብ መስራት ያዝኩ:: ሰርቼ ስጨርስ የትልቅ ሰው ሹራብ በአስር ብር፣ የልጅ ደግሞ በአምስት ብር እሸጣለሁ::

የንግዱ ነገር ውስጤ እየሰረፀ፣ ንግዴም ከዕለት ወደዕለት እመርታ እያሳየ መጣ::

በዚህም ለራሴ ሳንቲም መያዝ ጀመርኩ:: እንደ እህቶቼና የዕድሜ እኩዮቼ ባልዘንጥም መሠረታዊ ፍላጐቶቼን ማሟላት ቻልኩ:: የወደድኩትን ጫማ ገዛሁ፤ ብርድ ልብስም እንደ አቅሚቲ ሸመትኩ::

* * *

እኔ በሥራ መበርታት በጀመርኩበት ወቅት አያቶቼ በጉልበትም በገንዘብም እየተዳከሙ መጡ:: ዕድሜያቸው መጨመሩ ጉልበታቸውን፣ የነበራቸው የጠጅ ንግድ ቤት መዘጋቱ የገንዘብ አቅማቸውን አዳከመባቸው:: የእኔ ሥራ ግን እየዳበረ ሄደ፤ በየጊዜው አዳዲስ ሃሳቦች እያፈለቅኩ መሞከሩን ልምዶ አደረግኩት::

በመሐል ይመጡልኝ ከነበሩት ሐሳቦች አንዱን መርጬ እዚያው እነ እማዬ ግቢ ውስጥ ፊልተር ጠላ እያወጣሁ መሸጥ ያዝኩ:: ጠላው ቤት ተገብቶ የሚጠጣ ሳይሆን ደንበኞች ባመጡት ዕቃ ይዘዉት የሚሄዱና እቤታቸው ወይ እፈለጉበት ቦታ ሆነው የሚጠጡት ነው:: ከዚህም ሌላ





አባዬ በፈቀደልኝ ትንሽ መሬት ቆስጣ እያሳደግኩ ከመሸጥም አልፎ ከቆስጣው ላይ እንደ ልባችን መመገብ ጀመርን::

እነ አባዬ እንዲህ በየእቅጣጫው በተዳከሙበት ሰዓት ከማገኘው ገንዘብ የሚጐድላቸውን እሞላላቸውም ነበር:: አልፎም ተርፎ ሌሊት ሰባት ሰዓት ተነስቼ በድቅድቅ ጨለማ ከቤት እወጣና ከእንጦጦ ማርያም በላይ በኩል ኤልያስ አካባቢ ሄጄ ቅጠል ለቅሜ እመጣላቸዋለሁ:: የማገዶ እጣና ሲያስፈልግ ሄጄ ገዝቼ፣ ተሸክሜ የማመጣው፣ የምፈልጠው እኔው ራሴ ነበርኩ:: ዳቦ ለመግዛት በሌሊት ዘጠኝ ሰዓት ቀበሌ ወረፋ እይዛለሁ:: አብዛኛውን ነገር ከቀበሌ - ያውም በእታካች ወረፋ ፍዳ ተቆጥሮ በሚሸመትበት ወቅት - አምሳ ኪሎ በቆሎ ከቀበሌ ገዝቼ ወደ ቤት የማደርሰው እኔው ተሸክሜ ነበር:: ወደ ወፍጮ ቤትም ወስጄ አስፈጭቼ እመልስ ነበር:: መብራቴ፣ ዕድገት በህብረት ዘመቻ በመሄዷ የቤቱም ጠቅላላ ሥራ እኔ ትከሻ ላይ ነበር የወደቀው:: በዚህም በተለይ ሹራቦችን ለመስራት የቀኑ ሰዓት አልበቃ ብሎኝ ማታ ማታ እንቅልፌን እየተጋፋሁ መስራት ግዴታዬ ነበር::

እንዲህ የማደርገው እነማዬን መርዳት የኔ ኃላፊነት እንደሆነ አምኜም ተቀብዬም ነው:: ነገር ግን "ጉሽ! ልጃችን ደረሰችልን፣ እደጊ" የሚል በልፋቴ መርካት አላይባቸውም:: ይልቁንም አምሽቼ ስሰራ በርቶ የሚቆየው አምፑላቸው እያሳሰባቸው መብራት እያጠፉ ያሰናክሉኝ ገቡ:: የእኔ ብርታት ለእነሱ ምናቸውም አይደለም፤ የማደርግላቸውን አመስግኖ የሚቀበል ንፁህ ልብ አልታደሉም::

የመብራት ቆጣሪ እያጠፉ ሲያማርሩኝ በሻማ መሥራት ቀጠልኩ:: መቼም አንዴ ለከፋት የተነሳ ሰው ሰበብ አያጣም፤ "ቤታችንን ታቃጥይብናለሽ" ብለው በሻማ መስራቱንም ከለከሉኝ::

ሲፈጥራቸው እንዲህ ናቸው! ይሄ የማይለወጥ ተፈጥሮአቸው ነው:: ሆኖም ይህ ክልከላቸው አንድ መግደል የማይችለው ነገር ልቤ ውስጥ አለ - እሱም ሠርቶ የማደግ ጽኑ ፍላጐቴ ነው:: ይህ ጽኑ ፍላጐቴ ይባስ አብሮኝ በኖረው እልሄ ምክንያት እየተቀጣጠለ ሄደ::

በዚያ ጣጠኛው አብዮት መፈንዳት የተነሳ ኮሎኔሉ የእንጀራ አባቴም ታሰሯል:: ይሄ ሰው ቀለበት አስሮላት ኮሪያ ዘምቶ ሲመለስ ወልዳ የጠበቀችውን እናቴን መልሶ በክብር የተቀበላት ትልቅ ሰው ቢሆን ነው! እርግጥ እናቴ እጅግ ባለሞያ ነበረች፤ በዚያ ላይ ሲበዛ ቆንጆ:: አያቶቼ እንደሚሉት ከሆነ ከመታመሟ በፊት የሷን ሽማግሌ ማስተናገድ አቅቷቸው ነበር:: በሳምንት አራት አምስት "የልጃችሁን ስጡን" ሽምግልና ይመጣባቸው እንደነበር ይናገራሉ:: ነገር ግን ምን ባለሞያ፣ ምን ቆንጆ ቢሆኑ በሽታ ያስንቃል:: እናቴ ትንሽ ነገር ሲጐድልባት እንስቶ ከግድግዳ ጋር ያጋጪታል፣ ይፈነክታታል:: በሽታው በየጊዜው ጭንቅላቷን ወይ



Scanned with CamScanner

ሊሰማኝ እንደቻለ አላውቅም። ብቻ በደስታ ሮጬ ሄጄ ተጠመጠምኳቸው። ሁለቱም ጥቁር በጥቁር ለብሰዋል። በወቅቱ ጥቁር ልብስ ለምን እንደሚለበስ ግንዛቤው አልነበረኝም።

"ለምን ሄድኩ ሳትይ ውልቅ ብለሽ ጠፋሽ?" አሉኝ።

"እግሬ አብጦ አላሳከማችሁኝም፤ ደመወዜንም አልሰጣችሁኝም። ታድያ ምን ላርግ?" አልኳቸው።

እርስ በርስ ተያዩና ሳቅ አሉ። ከዚያ "አሁንስ ከእኛ ጋር አትሄጂም?" አሉኝ።

"አይ፣ አልሄድም።"

"ለምን?"

"ሥራችሁ ብዙ ነው፤ እግሬ ያብጥብኛል።"

"በይ እሺ. ለዛሬው ከኛ ጋር ውለሽ አድረሽ ነገ ትመለሺያለሽ። ልጆቻችን ናፍቀውሻል" አሉኝ።

በሃሳባቸው ተስማምቼ ወደ መኪናቸው ልገባ ስል የደላላው ቤት ጓደኞቼ፣ "ዘመዶችሽ ናቸው? ሥራ ልትገቢ ነወይ?" እያሉ ተንጫጩ።

"አይ፣ ዕቃ ላመጣ ነው። ነገ እመጣለሁ፣ ጠብቁኝ" ብያቸው ከሰዎቹ ጋር መንገድ ጀመርኩ። ቤት ስደርስ ልጆቻቸው በእኔ መምጣት ተደስተው ቦረቁ። ይሄን ሳይ ደስታም ሀዘንም ወረረኝ። ፍቅር የማላውቅ፣ በፍቅር እጦት የተጐዳሁ ሰው ነኝና የሚወደኝን ሳገኝ በኃይል ተደስቻለሁ፤ ቤተሰቦቼ እንደዚህ ቢወዱኝ ምን ነበረበት? ብዬ ደግሞ ማዘኔና መተከዜ አልቀረም። ብቻ ከሀዘኑ ይልቅ ደስታዬ አይሎ ነበር።

በወቅቱ ሌላው የገረመኝ የመኖሪያ ቤታቸው ማማር ነው። በሕይወቴ እንደዚያ የሚያምር ቤት አይቼ ስለማላውቅ ፍፁም ተደንቄ ነበር። የእንጀራ አባቴ ባለ ስልጣን በነበረበት በዚያ ደጉ ዘመን የነበራቸው ቤት ለካ ከዚህ ጋር ሲወዳደር ኢምንት ኖሯል!

የእትዬ ዘነቡ ልጆች ተመልሼ ትቻቸው እንዳልሄድ አብዝተው ለመኑኝ። በዚያን ጊዜ እዚያ ቤት ላለመቆየት የወሰንኩበት ሁነኛ ምክንያቴ ምን እንደነበር አሁን ትዝ አይለኝም። ብቻ እዚያ ቤት ለመቆየት አልፈለኩም። ደግሞም በሆነ ምክንያት ቅር ቅር ብሎኛል።... ወዲያው ትዝ አለኝ። ቤቱ ውስጥ አንድ ነገር ጐድሏል። ኤልሳ ልጃቸው የለችም። "ኤልሳስ?" ብዬ ጠየቅኩ። በድንገተኛ ህመም በሞት እንደተለየቻቸውና ሀዘን ላይ እንደሆኑ ነገሩኝ። አለቀስኩ። በእውነት እወዳት ስለነበር ድምጽ አውጥቼ አለቀስኩ።

በነጋታው እትዬ ዘነቡ ከልጆቻቸው ጋር ሆነው አብሬያቸው እንድኖር በድጋሚ ለምነውኝ እምቢ ስላቸው የሰራሁበትን እጥፍ ገንዘብ ሰጥተው ሸኙኝ።

* * *





ደላላው ቤት እግዜር ለእኔ ያላቸው ጥሩ ሰዎች መጥተው ሥራ እስኪቀጥሩኝ ድረስ ሹሩባ መስራቴን ተያያዝኩት። በየቀኑ ሁለትም ሦስትም ሠርቼ ለምበላውና ለአዳር ለምከፍለው አገኛለሁ።

ሌሎቹ ሥራ ፈላጊ ሴቶች ግን ቀጣሪ እስኪያገኙ ሥራ ፈትተው ቁጭ ብለው ሲያወሩ፣ ሲያልቅባቸው ሲተክዙ፣ ባዩት ነገር ሁሉ ሲስቁ፣ በሆነው ባልሆነው ሲገለፍጡ፣ ሆድ ብሷቸው ሲላቀሱ ነው ውለው የሚያድሩት። እኔ ግን ሥራ ሱስ ሳይሆንብኝ አይቀርም - መቀመጥም አልወድም። ፀጉር ሥራ በሌለኝ ሰዓት እንኳን ከእነሱ ጋር ሥራ ፈትቶ ወሬ ከማቡካት ደላላ ቤቱን ማፅዳት እመርጥ ነበር።

ውሎአችን እንዲህ እንዲህ ሆኖ ብዙ ሳልቆይ አቶ ድንቁ የሚባሉ ሰውዬ በመደዳ ከተቀመጥነው ሴቶች ባጋጣሚ እኔን መርጠው ወደ እኔ አቀኑ። ሥራው ለአንድ ቡና ቤት ብርጭቆ ማጠብ መሆኑን ሲነግሩኝ፣

"እኔ ቡና ቤት አልገባም" ብዬ ተቃወምኳቸው።

"ኧረ ትንሽዬ ቤት ናት፤ የሚያውቅ ሰው ካልሆነ ሰው አይበዛባትም። ደግሞ ያንቺ ሥራ እንዳልኩሽ ብርጭቆ ማጠብ ብቻ ነው። እንዳንቺ ያሉ ልጆች አሉኝ፤ ቤተሰብ ትሆኛለሽ።" ሲያግባቡኝ ሞከሩ። ከብዙ ማግባባት በኂላ በሃያ አምስት ብር ወርሃዊ ደመወዝ ልሰራ ተስማምቼ አብሬያቸው ሄድኩ።

በመንገድ ላይ እንደ ማግባባትም እንደ መምከርም እየቃጣቸው ያዋሩኝ ነበር። "እንዳንቺ ዓይነት ልጅ ነው እኛ የምንፈልገው" ሲሉኝ የት አውቀውኝ ነው?! ብዬ እየተገረምኩ አዳምጣቸኂለሁ። ደግሞ ይቀጥሉና "አይዞሽ፣ አንቺ ልጅ ስለሆንሽ ፈላጊሽ ብዙ ነው፤ ካወቅሽበት በደንብ ትጠቀሚያለሽ" ይሉኛል።

ሃሳባቸው ገብቶኝ አዘንኩባቸው፤ አለቀስኩም። "እኔ እርስዎ እንደሚያስቡኝ አይነት ልጅ አይደለሁም፤ ገና ከቤቴ የወጣሁ ልጃገረድ ነኝ። ከቤቴም ያወጣኝ ችግር እንጂ ጥጋብ አይደለም።"

"ኧረ እኔ...." ሊያረጋጉኝ ሞከሩ።

"አይ ሃሳብዎ ይህ ከሆነ በቃ አገኙኝ ቦታ ይመልሱኝ" አለቀስኩ።

"አይዞሽ፣ የእኔ ልጅ። ምን ዓይነት ሴት እንደሆንሽ ልገምት ብዬ እንጂ እውነቱን መስሎሽ ነው እንዴ?"

እንዲህ እያባበሉኝ ሥራ ወደምጀምርበት ቤት ደረስን። ሰፈሩ በሜክሲኮና በገነት ሆቴል መካከል በተለምዶ "ትንሹ ሽመልስ" ተብሎ ከሚጠራው። "ሽመልስ ሀብቴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት" ከፍ ብሎ የሚገኝና ካምቦኖቦ የሚባል ሠፈር። የከባድ መኪና ጋራዦች ይበዙበታል።

ከቡና ቤቱ ባለቤት፣ ከወ/ሮ ምንዳዬ ጋር እንደተገናኘን ወዲያው "መጀመሪያ ሥራዬ ምን እንደሆነ ማወቅ እፈልጋለሁ" ስል ጠየቅኳት።



Scanned with CamScanner

ጉዳት በሌሎች ልጆቿ ላይ እንዴት ነው የማይሰራው? ይሄ በምንም መልኩ ሊዋጥልኝ የማይችል ሰንካላ ምክንያት ነው፡፡

ከእንግዲህ እኔና እናቴን አስማምቶ የሚያስቆየን ነገር ቢኖር መራራቅ ብቻ ነው፡፡ ሁለታችንም በሰላም መኖር ካለብን እንደ እሳትና ጭድ ተራርቀን ልንኖር ግድ ነው! እንዲያውም እያቶቼ መጥተው "እስከ ክርስትናው እስኪያልፍ ይህን ሁለት ቀን ታገሺ" ብለው ባይማፀኑኝ ኖሮ የእናቴን ቤት ጥዬ ለመውጣት የወሰንኩት ዛሬውኑ ነበር፡፡

በመጨረሻም የመከራረፍና በከፋ የመተያየት ቀናት አልፈው የክርስትናው ቀን ደረሰ፡፡ ብቀየማትም ቃል ነበረኝና ክርስትናውን ለመሰረት ሰጠኋት፡፡ ድግስ ደግሼ ወዳጆቼ ያልኳቸውን ሁሉ ሳስተናግድ ዋልኩ፡፡

ከንግዲህ እናቴ ቤት ለመቆየት የሚያስችለኝ አንዳች ምክንያት የለም፡፡ በቃ - የቆረጥኩት ቀን ይሄ ነበር፡፡ መብራቴ "አንቺ ሥራ ይዘሽ ቤት ተከራይተሽ፣ አንዳንድ ነገሮችን እስክታስተካክይ ድረስ ልጅሽን እኔ እጠብቃታለሁ፣ ምዕራፍም አለችላት" ስትለኝ ስጋቴ ተቀንሶ ልጄን እዛው ትቼያት በማግስቱ የእናቴን ቤት ለቀቅኩ፡፡





# ክፍል አምስት

# እናትነትና ሠርቶ የማደር ትግል

## - 1 -

በወሊድና በተደራረቡብኝ ተከታታይ ችግሮች ምክንያት ሰውነቴ አልቆ አጥንቴ ወጥቷል፡፡ ጡት ሳጠባት ስላልቻልኩ ልጄም እንደኔ በኃይል ተጐድታለች፡፡ ስለዚህ ልጄን ለሞግዚት ሰጥቼ ሥራ መቀጠር እንዳለብኝ ወስኜ፣ ቢያንስ ለሞግዚትና ለልጄ ወተት መግዣ ገንዘብ ልጠይቀው ቀጥታ አርአያ ወደሚገኝበት የእነ መሰረት ሆቴል ሄድኩ፡፡

ስደርስ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሆኗል፡፡ ጠይቄ በተነገረኝ መሠረት የተኛበት ክፍል ድረስ ሄጄ በር አንኳኳሁ፡፡ "ማነው?" አለኝ፡፡ ድንገት እሱ ጋ መምጣቴ ምን ሊሰማው እንደሚችል ለማወቅ ፈልጌ ድምፅ ሳላሰማ በድጋሚ አንኳኳሁ፡፡ አሁንም "ማነው?" ከማለት በስተቀር በሩን ሊከፍትልኝ ሳይሞክር ቀረ፡፡ እንደገና አንኳኳሁ፡፡ ይኸኔ በስጨት ያለ የአንዲት ሴት ልጅ ድምጽ "ማነው?" ሲል ሰማሁ፡፡ ንዴት እያንዘረዘረኝ ወደ ኋላ ተመልሼ ኮሪደር ላይ ተቀመጥኩ፡፡

ከጥቂት ቆይታ በኋላ በሩ ተከፈተ፡፡ እዛው ሆቴል ውስጥ የምትሰራ፣ በጣም የምግባባትና እንደ ጓደኛ የምቀርባት ሴት ከክፍሉ ወጣ እንዳለች አየችኝ፡፡ ክው አለች፡፡ እንደሚመስለኝ የሆነ ቦታ ለመደበቅ ወይም ወደ ክፍሉ ተመልሳ ለመግባት አስባ ላፍታ እንደ ማመንታት አለችና ድንብርብሩ በወጣ ፈጣን እርምጃ ወደኔ አቅጣጫ ስትመጣ አየኋት፡፡ ሰላም ልትለኝ ድፍረት አጥታ አንገቷን እንደደፋች ካጠገቤ ልትርቅ ስትል ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ሰላም ብያት ወደ ክፍሉ ዘለቅሁ፡፡ ባየሁት ሁኔታ ባዝንም፣ ያየሁትን ስለማየቴ አርአያ እንዲያውቅ አልፈለግኩም፡፡ ቀጥታ ወደመጣሁት ጉዳይ ገባሁ፡፡

"አንዳንድ ጥያቄዎች ልጠይቅህ ነበር?"

"ፖሊስ ነሽ እንዴ ጥያቄ የምትጠይቂኝ?" አለኝ ለመቀለድ እየሞከረ፡፡ ይሁንና ከንፈሮቹ ዙሪያ ሃፍረት፣ ዓይኖቹ ውስጥ ደግሞ ድንጋጤ ይስተዋልበታል፡፡ ያፈረው ምናልባት ልጅቷ ከዚህ ክፍል ውስጥ



Scanned with CamScanner

ወረፋዋ ደርሶ ሀኪሟ ጋ ስንቀርብ፣ "ሶስት ወር ያለፈው ስለሆነ አደጋ ሊኖረው ይችላል። መጀመሪያ እስፔሻሊስት ማማከር አለብን" አለችን።

እህቴ ክው ብላ ቀረች። ልደታ ማርያም እስክንደርስ እያለቀሰች ዕድሏን ታማርር ነበር።

"ምንም ነገር እንዳታደርጊ በዚች በእመቤታችን ስም ቃል ግቢልኝ! ማስወረዱ አደጋ አለው ስለተባለ ይህን ነገር በፍጹም መሞከር የለብሽም" አልኳት።

"ቤተሰቦቼስ...? የቤተሰቦቼ ነገር እጅግ አስፈርቶኛል'ኮ" አለችኝ እየተነፋረቀች።

"ስለእነሱ አታስቢ። እኔ ዘዴ አዘጋጅቻለሁ።"

"ምን ዓይነት ዘዴ?" አለችኝ በጉጉት ዓይን ዓይኔን እያየች።

"መጀመሪያ ቃል ግቢልኝ!"

"እሺ..."

"ማንም እዚህ ቦታ ይሳካልሻል ቢልሽ አትሄጂም?"

"አልሄድም! አላስበውምም።"

ድጋሚ ቃል ካስገባኋት በኋላ ሌሊቱን ሙሉ ሳስብበት ያደርኩትን ነገር በዝርዝር ነገርኳት። እስክትወልድ ድረስ ራቅ ያለ ሰፈር ቤት ተከራይቼላት አቅሜ የፈቀደውን ሁሉ እንደማደርግላት፣ ከወለደችም በኋላ ህፃኑን ወስጄ እንደ ራሴ ልጅ ላሳድገው ብችል ደስተኛ እንደምሆን ስነግራት በንግግሬ መሀል ጣልቃ ገብታ፣

"ቤተሰቦቼስ...? ያን ሁሉ ጊዜ ጠፍቼ ስከርም አይጨነቁም...? በጭንቀት አገር ምድሩን አይበጠብጡትም..." ስትል ስጋቷን በጥያቄ መልክ አጋራችኝ።

"የነሱ ነገር አያሳስብሽ። ቀላል ነው። ...ይኸውልሽ የሆነች ሴትዮዋ ከዚህ ቀደም ‹እሩቅ ባይሆንብሽ እኔ ጋ ትገቢ ነበር› ብላኝ ስለነበር መጀመሪያ እኔ ዛሬውኑ እሷ ጋ እሄድና የሚከራይ ባዶ ክፍል እንዳላት እጠይቃታለሁ። ግን የሴትዮዋን መልስ እስከምናገኝ ምንም ነገር እንዳታደርጊ። እኔ እስከ ዛሬ ማታ አሳውቅሻለሁ። ሴትዮዋ ቤቷን ልታከራየን ፍቃደኛ ከሆነች አንቺ ወዲያውኑ ለቤተሰቦችሽ ‹ሥራ አግኝቼ ራቅ ወዳለ ቦታ ስለሄድኩ አታስቡ፤ እዛ ስደርስ ያለውን ሁኔታ በሙሉ እጽፍላችኋለሁ› በማለት ደብዳቤ ጽፈሽ ታስቀምጪና ለማኝ እንትን ሳይል ሁለት ቅያሬ ልብስ ብቻ ይዘሽ ማንም ሰው ሳያይሽ በድብቅ እኔ ጋ ትመጪያለሽ።"

"ከዚያስ?"

"ከዚያማ በየወሩ ከደመወዝሽ ላይ ተቆራጭ እንደላክሽ በማስመሰል ወደ ቤት እንልካለን - ከእግዚአብሔር ጋር እኔ እሰጥሻለሁ።"





"ውይ አስት! ውለታሽ በጣም ከባድ ነው - መመለስ የምችል አይመስለኝም።"

"እሱን ተይውና...ይልቅ ያሰብኩትን ልጨርስልሽ። እናም በሰላም ወልደሽ ጥቂት እንደቆየሽ - ከፈለግሽ ‹ሥራው ስላልተስማማኝ ተመልሼ ወጣሁ› በማለት ወደቤትሽ መግባት ትችያለሽ። እንዴት ነው ያስኬዳል?"

"በጣም አሪፍ ሃሳብ ነው እንጂ! የሚገርም ነው! እንዴት አሰብሽው?"

"እስከዚያው ማንም ሰው ምንም ነገር መስማት የለበትም። ሁለታችንም ምስጢር ጠባቂ መሆን አለብን። አለዚያ አደጋ አለው። ገብቶሻል አይደል?"

"ገብቶኛል" አለች።

ሁለታችንም በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ቃሉ-መሃላ ከፈፀምን በኋላ በመጨረሻ ወደሌላ ጥያቄ ዞርኩ።

"ለመሆኑ ያረገዝሽው ከማን ነው? አሁንም ታገኚዋለሽ?" ጠየኳት።

"አዎን፤ ሥራው አምቦ ጉደር የሚባል አገር ነው። በሚቀጥለው ሳምንት ይመጣል።"

በዚህ ሰዓት ስለፍቅረኛዋ ከዚህ በላይ ጠይቄ ላስጨንቃት አልፈለኩም።

ጧት አልጋና ሌሎች አስፈላጊ ዕቃዎችን ገዛዝቼ እተከራየሁላት ቤት ካስገባሁላት በኋላ የዚያኑ ዕለት ለዓይን ያዝ ሲያደርግ ወደተከራየሁላት ቤት ወሰድኳት። ከቤት ወጥታ የማታውቅ፣ እንደ እኔ ችግርን ያልቀመሰች፣ በድሎት የኖረች ልጅ ስለሆነች ለመጀመሪያ ጊዜ ከቤቷ ስትወጣ ሊሰማት የሚችለውን ነገር ሁሉ እያሰብኩ ተረበሽኩ። አዲሱ ቤቷ የደረስነው እኔም እሷም እያለቀስን ነበር። በዚያ ሁሉ መንገድ ምንም አልተነጋገርንም ማለቱ ይቀላል። እኔም እሷም ቤት ምን እንደሚባል፣ ምን ያህል እንደሚጨነቁ በማሰብ ሀይለኛ መረበሽ ውስጥ ተዘፍቀን ነበር። ይህ የወሰድነው እርምጃ በርግጥ ትክክለኛ እርምጃ ይሆን? እንዳሰብነው በሰላም ወልዳ፣ በሰላም ወደቤቷ ትመለስ ይሆን? የዚያ የሚወለደው ህፃን ልጅ ዕጣ ፈንታስ ምን ይሆን?

ወደተከራየሁላት ቤት ደርሰን ካስገባኋት በኋላ መሽቶ ስለነበር ነገ እንደምመጣ ነግሬያት፣ ለአንዳንድ ወጪዎች ፍራንክ በእጇ ሰጥቼያት ለሴትዮዋም በለቅሶ በተሰባበረ አንደበት "አደራ እንደ ልጅሽ እያት። ከቤት ወጥታ ስለማታውቅ እንዳይቸግራት አደራሽን ተከታተያት" ብያት እያለቀስኩ ቤቴ ደረስኩ።

ቤቴ ስገባ አያቶቼ ስለመጥፋቷ የማውቀው ነገር እንዳለ ሊጠይቁኝ መጥተው እንደነበር ሰማሁ። ጭንቀቱና መረበሹ፣ ሙሉ ሙሉ ካልለቀቀኝ ህመሜ ጋር ተደማምሮ በኃይል ድካም ቢጫጫነኝም፣ እንደሰማች ለምን

"ወይ ጣጣ! የቀጠሮውን ቀን፣ ቦታና ሰዓት እኮ እኔ አይደለሁም የወሰንኩት። እነሱ ራሳቸው ናቸው። ከዚህ ወደ ቀጠሮው ቦታ ሲወስዱኝ ቀጠሮው ዋቢ ሸበሌ ይሁን ሌላ ቦታ የማውቀው ጉዳይ አልነበረኝም። ኧረ ለመሆኑ ምንድው ችግራችሁ? ሱዳኑ ምንድነው? ለአባቴስ ምን ብሎ ነው የተናገረው? ዳር ዳር ከምትሽከረከሩ ለምን ግልጹን ፍርጥ አድርጋችሁ አትነግሩኝም? ምን አስፈራችሁ?"

ሊነግሩኝ አልፈለጉም። እነዚህ ሰዎች ስለምንድ ነው የሚያወሩት? እውነት ከልባቸው ነው ወይስ ቀልድ ነው የያዙት? የምራቸውን ከሆነ ጉዳዩ ቀላል አይሆንም። ጭንቀላቴ በሐሳብ ሲወጣጠር ይታወቀኛል። የዚህ ጉዳይ ቁልፉ ያለው አባቴ እጅ ላይ ነው።

መቼም በእኔ የማይበረታ የለም። ባልዋልኩበት መጠየቅ፣ ባልሠራሁት መከሰስ ልማዴ ነው። ይህ የዕጣ ፈንታዬ ያህል ተጣብቆብኝ ያለ በደል እዚህም ተከትሎኝ መጣ ይሆን? እያልኩ ሐሳብ ሳመናትል አባቴ ነቃ። አዳሩንና ጤንነቱን ጠየቅኩትና የከነከነኝን ጉዳይ አነሳሁበት፣

"ሱዳኑን ከዚህ ቀደም ታውቀው ነበር?"

"አላውቀውም።"

"ትናንት ምን ብሎህ ነው የተረበሸከው?"

"ምንም አዲስ ነገር አልነገረኝም፤ አስቀድሜ የማውቀውን ነገር ነው መልሶ የነገረኝ።"

"ታዲያ እንዴት እንደ አዲስ ወሬ ሊረብሽህ ቻለ?"

በትዕዝብት አየት አድርጎኝ ዝም አለ።

"ለመሆኑ ምንድነው የነገረህ?"

"የሆነ ነገር ነግሮኛል።"

"እኮ ምን የሆነ ነገር?"

"የሆነ ነገር ካልኩሽ አይበቃም?!" አለኝ ቀዝቀዝ ብሎ። ስለሱዳኑ ከዚህ በላይ ማውራት አለመፈለጉ ሲገባኝ ተሰናብቼው ወጣሁ።

❋ ❋ ❋

አባቴ እንዳሰብኩት እንቆቅልሽ የሆነብኝን ጉዳይ የሚፈታልኝ ቁልፍ አልሆነም። በርግጥም ነገሩ እውነት ሳይሆን አይቀርም። እውነት ከሆነ ደግሞ ብዙ መዘዝ ሊያማዝዝ ይችላል። ወይ መከራዬ... እንዲህ በሃሳብ እየተብሰለሰልኩ ሳይታወቀኝ በእግሬ ብዙ መንገዴን ያስተዋልኩት የተፈሪ መኪና ጡሩንባ እላዬ ላይ ሲያንበባርቅ ነበር።

"እንደዚህ በየመንገዱ የሚያፈዝሽ ምን ከባድ ሃሳብ ቢሆን ነው? ነይ በእግርሽ ከምትሄጂ አባትሽ ጋር ደርሰን እሸኝሻለሁ" አለኝ።

መኪናው ውስጥ ገባሁ።

"ምን ሆንሻል?" አለኝ ተፈሪ ቅዝዝ ማለቴን ተመልክቶ።





"ምንድነው ነገሩ፤ ልጆቹ በሱዳን በኩል አስተካክለሽ ቅብርጥሴ አሉኝ። እሱንም ስጠይቀው ሊነግረኝ አልፈለገም"

"ተይው፤ እርሺው። ስለህይወትሽ ብቻ አስቢ."

ተፈሪም በግልፅ ሊነግረኝ የፈለገ ስላልመሰለኝ ከማስጨንቀው ብዬ በጥያቄዬ ሳልገፋ ቀረሁ። እሱም ርዕሱን ቀይሮ ስለትናንቱ ቀጠሮ አነሳብኝ፡-

"ምን አሰባችሁ?" አለኝ።

"አባቴ ካንተ ጋር እንደሚነጋገርና ሌላ ቀጠሮ እንደምንይዝ ነግሮኛል" ብዬ መለስኩለት።

እያወራን አባቴ ቤት ደረስን። እሱ አባቴ ጋ ሲገባ እኔ ደግሞ ከወንድሞቼና ከእንጀራ እናቴ ጋር ተቀመጥኩ። ወሬው እንደ አዲስ ተነሳ። አሁን የጀመረችው እትዬ ማርታ ናት።

"እውነት ግን ሱዳኑን ካሁን በፊት አታውቂውም?"

"አላውቀውም!" ነገሩ እያበሳጨኝ ሳይመጣ አልቀረም። "እናንተ ግን እንዲህ ያስጨነቃችሁን ነገር ለምን በግልጽ አትነግሩኝም?"

"በፊት የተመረቀበት ቦታ ትንቢት ተነግሮታል" ብላ እትዬ ማርታ ከመናገሯ ወንድሜም ጣልቃ ገባ፡-

"የተነገረው ትንቢት አንቺ የተወለድሽበት ቀን አልቀረውም። ለዚህ እኮ ነው ምልክቱን ሲነግረው ያወቀው።"

በመሃል አሰላሰልኩ። ሱዳኑን ማግኘት ቢቻል ነገሮች ይስተካከሉ ይሆናል። ግን እሱን እንዴት መልሶ ማግኘት ይቻላል? አድራሻውን ያውቁት ይሆን?

"ታዲያ ይህን ሱዳን እንዴት ድጋሚ ማግኘት ይቻላል?" ብዬ ከመናገሬ አሁንም ወንድሜ ተሽቀዳድሞ፣

"እንዴ! ምን ትጠይቂናለሽ? እንደምታውቂው ትሄጃለሽ፤ ታገኚዋለሽ" አለኝ።

ንዴቴ ጣሪያ ነካ። ሽሙጡ አበሳጨኝ።

ተፈሪ ከአባቴ ጋር የነበረውን ጉዳይ ጨርሶ ሲመጣ የመጨቃጨቅ ያህል ስናወራ አገኘን፤ ሁኔታችን አስገርሞት "ምንድነው?" ብሎ ጠየቀን። በዝርዝር ነገርኩት። አዘነ።

"የቀጠሮ ቦታውን የመረጥኩት እኔ ነበርኩ። ደግሞም ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ከትናንት በፊት በበሩ ከማለፍ ውጪ ውስጡን አይቼው አላውቅም" አላቸውና ሊሸኘኝ ተያይዘን ወጣን። መንገድ ላይ የውጪውን ንግድ ለማከናወን ፕሮሰሱን እንዴት ማስኬድ እንዳለብኝ በድጋሚ መከረኝ።



Scanned with CamScanner

# ክፍል አሥራ አንድ

# ስንብት

## - 1 -

የአባቴን ድርጊት የማዛምደው ከቆሳሰልኩበት የልጅነት ዘመኔ ጋር ነው። ያኔ በእያንዳንዱ የቁስል ጠቃጠቆዬ ላይ እንዳከው የሚጉተጉተኝ ስሜት ነበረብኝ። የቱን አክኬ የቱን? አንዳንዴ በመደዳ እየፈተኩ አካላቴን ለማዳረስ እሞክር ነበር። ወይም ባገኘሁት በድንጋይም ቢሆን ገላዬን አዳምጠዋለሁ። አባቴም ነፍሴን አቆሳስሎት የገላዬን ያህል ማከክያ ጥፍር አጣለታለሁ። "ትፈልኝ" ብሎኝ እምቢ ካልኩት በኋላ ነፍሴን ውሃ እንዳዘለ ቁስል እየነዘነዛት ነው።

በየትኛው በኩል ልጠብቀው? ዱርዬውን፣ ሰካራሙን፣ የመንግሥት ሠራተኛውን፣ ፖሊሱን፣ ወታደሩን... ነገርና ገንዘብ እያስታጠቀ ይልክብኛል። ፋይዳው ምን እንደሆነ ባይገባኝም እንደ ቄስ ወይም እንደ ኢማም አናታቸው ላይ የጠመጠሙ የኃይማኖት ሰዎችን ሳይቀር እቤቴ ደጃፍ እያስቆመ ነፃነት ሊያሳጣኝ ይሞክራል።

በየት በኩል መጥቶ በምን ሊያጠቃኝ እንደሚችል ሳስብ ግራ እጋባለሁ። ትራፊክ ፖሊሶች ሳይቀሩ "ተጠቁሞብሽ ነው" እያሉ በየአደባባዩ ደጀ ያስጠኑኛል። እኔን ለማሳዘን እህቴን የትናየትን መልሶ ወስዶብኛል። እኔጋ ህመሟ ተሽሏት የተረጋጋ ህይወት መኖር ጀምራ ነበር።

አሁን ደግሞ ብሎ፣ ብሎ የፈታሁትን ባሌን ተወዳጅቶ ቅንጅት በመፍጠር ያስጨነቀኝ ይዟል፤ በእኔና በባለቤቴ መሃል ተፈጥረው የነበሩ የትዳር ግጭቶች እየተካረሩ መጥተው በ1991 ዓ.ም የመስቀል በዓልን ባከበረን በሳልስቱ የፍርድ ቤት ሰማንያችንን ቀደድን። ከቤቱ ውጭ ያለውን ሃብት ሁሉ አካፍዬዋለሁ። ነገር ግን እሱን ሳገባ አባቴ የሰጠኝን ሽጉጥ ጠይቶኝ ሳልሰጠው በመቅረቴ ቅሬታ አሳድሮ ከአባቴ ጋር ተወዳጅቷል። ግንባር የፈጠሩት አባቴና የቀድሞ ባለቤቴ እኔን የሚጐዱበትን ዕቅድ ሲያወጡ ሰንብተው በአዲስ መልክ ይበጠብጡኝ፣ ያንገላቱኝ ጀመር።

አባቴ ቤት ያገለግል የነበረና አባቴ አምርሮ የሚጠላው ፀሐዬ የሚባል ሰው ከአንድ ኤርትራዊ ጓደኛው ጋር እኔ ቤት መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ሆኖአቸዋል። እናም ልክ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በተቀሰቀሰበት ሰሞን ፖሊሶች የመኖሪያ ቤቴን በር አንኳኩተው አስጠሩኝ።





"ባለቤቷን እንፈልጋታለን"

"አቤት ምን ተፈጠረ? ችግር አለ እንዴ?"

"ኤርትራዊ ቤትሽ ውስጥ ደብቀሻል"

"አልደበቅኩም"

"ገብተን እንፈትሻለን"

"ማዘዣ አላችሁ?" ይሄኔ ተደናገሩ።

"ለማንኛውም ማዘዣውን ይዘን እንመጣለን" ብለው ሄዱ። አልተመለሱም።

እነዚህ ፖሊሶች ከወረዳ ሃያ አምስት የመጡ መሆናቸውን በሌላ ቀን መጥሪያ ይዘው ከመጡ ፖሊሶች ተረዳሁ። ወረዳ ሃያ አምስት ደግሞ አባቴ የሚኖርበት ወረዳ በመሆኑ፣ ሰዎቹ በእርሱ እንደተላኩ ገባኝ።

እናም ቤቴ ድረስ መጥሪያ ተልኮብኝ በተባለው ቀን ፖሊስ ጣቢያ ተገኘሁ።

"ተከሰሻል" ስባል ደነገጥኩ። አባቴ በፖሊስ እንደሚጠቀም ባውቅም ከሳሹ ይሆናል ብዬ አልጠረጠርኩም፤ ደግሞስ በምን ሰበብ ይከሰኛል?

በረንዳ ላይ ቁጭ ብዬ የሚሆነውን ስጠባበቅ አባቴ ገባ፤ ከተል ብሎት ባለቤቴ መጣ። አባቴ ቀጥታ ወደ መርማሪው ቢሮ ገባ። እሱ ሲወጣ እኔ ተጠራሁ።

"አቶ ሠይፉ የሚባሉ ሰው ‹ሽጉጥ ወስዳብኛለች› የሚል ክስ አቅርበውብሻል። የእሳቸው የሆነ መሣሪያ አንቺ ጋ አለ?"

ነገሩ ተገለጠልኝ። "ሽጉጡ አለ። ነገር ግን የሠርጌ ዕለት አባቴ ራሱ ለእኔና ለባለቤቴ በስጦታ ያበረከተልን ነው" አልኩት።

"አባቴ ስትይ ሰማሁ ልበል?"

"ልክ ነው። ከሰሰሽ ያልከው ወላጅ አባቴ ነው"

ፖሊሱ ተገረመ። "ታዲያ አባትሽ ከሆኑ ለምን ጉዳዩን እዚሁ ተነጋግራችሁ በሽምግልና አይፈታም?" አለ። ተስማማሁ። አባቴም ተጠርቶ ገባ። ባለቤቴም እንደጥላ ተከትሎታል። መርማሪው እኔና እሱ የተባባልነውን ነገረውና፣

"አባትና ልጅ ከሆናችሁ እዚሁ ብትነጋገሩና በሽምግልና ብትፈቱት ነው የሚሻለው" የሚል ሃሳብ አቀረበለት።

አባቴ በቁጣ ከመቀመጫው ብድግ አለ። "አይሆንም! ልጄ አይደለችም! እኔ አላውቃትም! መሣሪያዬን ሰርቃለች! እሱን ብቻ ትመልስልኝ" አለ።

እኔም በሁኔታው በስጨት ብዬ "ዛሬም ሆነ ነገ ካንተ ሌላ አባት የለኝም። አባቴ ስለመሆንህ ደግሞ በቂ ማስረጃዎችና ምስክሮች አሉኝ" አልኩ።

"መርማሪ፣ ለምን ጊዜዬን በእንቶ ፈንቶ ታባክንብኛለህ? መሣሪያዬን የማትመልስ ከሆነ መክሰስ ነው የምፈልገው አልኩህ እኮ!"



Scanned with CamScanner

*ቢሆንም ሩት ብዙ ይቀራታል። በዚያ ላይ ራሷን ፈልጋ ገና አላገኘችም። አንዴ ትያትር ሰሪ፣ ሌላ ጊዜ ገጣሚ፣ ሲላት የፊልም ተዋናይት፣ ወዲያው ደግሞ ዘፋኝ መሆን ያምራታል። እኔ በትምህርቷ ብትገፋ ነበር ፍላጐቴ። የእሷ ምኞት ግን በአቋራጭ እውቅናን ማግኘት ነው። ለቴሌቪዥን ማስታወቂያ የሚሆን ቀረፃ አድርጋ ስትመጣ፣ በቴሌቪዥን ግጥሟን ስታነብ፣ ሼክ ሙሐመድ አላሙዲንን የሚያሞግሰው ዘፈኗ በራድዮ ሲለቀቅ፣ በመጨረሻም የዘፈን አልበም ስታሳትም ወዘተ… የተሰማትና በፊቷ ላይ ይነበብ የነበረው ስሜት እላይ ላነሳሁት አይነተኛ ማሳያ ነው። ልጆ የራሷን ብቻ መንገድ የምትከተል ቆራጥ ልጅ ናት። እኔን ለማስደሰት ብላ የምታደርገው አንዳችም ነገር የለም። ይሉኝታ የለባትም። ግን…*

ምኞቷና ምኞቴ ሊቀበር መሆኑ ታወሰኝና ማንም የማይገባው የእናት ለቅሶ አነባሁ። ጠላቶቼን ለመዋጋት እንደማልችል ሳውቅ፣ አይዞሽ ባይ ረዳት እንደሌለኝ ስረዳ፣ ፖሊስም ሆነ ቀበሌ በደፈናው "እንከታተላለን" ከማለት ውጭ መከታ ሊሆኑኝ እንደማይፈልጉ ሲገባኝ፣ ነገር ዓለሙ ተምታታብኝ። ዞረብኝ። ኡኡታዬን የገደል ማሚቶ በላው። ጩኸቴን ደመናው ዋጠው። እንባዬን ምድር መጦ አስቀረው። በቃ! እምቧጮ እንኳ ባልበቀለበት በረሃ ውስጥ ለብቻዬ ከመከራ አሸዋ ጋር የምጋፋ ያህል ብቸኝነት ወረረኝ።

በዚህ መሃል የሆነ ድምፅ፣ የሆነ ነገር ሹክ ያለኝ መሰለኝ። ከወንበሬ ዘልዬ ተነሳሁና ሩታ! ሩታ! እያልኩ ወደቤት ገባሁ። ፊቴ በእፎይታ ፈካ። ልቤ መረጋጋትን አግኝቶ ሰከን ማለት ጀመረ። ልጄን የማድንበት ብቸኛው መንገድ ይሄ ነው። "በቃ፤ መደረግ አለበት" አልኩ። መጮሄ አልታወቀኝም።

"ምነው እማዬ፣ ደህና አይደለሽም እንዴ?"

"እ… ደህና ነኝ። ይሄውልሽ ሩትዬ፣ ከቤት ስትወጪ ፊትሽን በሻርፕ ሸፍንፍን አድርገሽ፣ እሺ? አደራ እትርሺ።"

"እሺ። መደረግ አለበት ያልሽው ይህንን ነው?"

ዝምታ!

አርቲስት ማሕሙድ አሕመድ እንዳቀነቀነው፡-

*"…ሾተሉ እስኪነቀል የነገር አንካሴ*
*የእውነት ፀሐይ ወጥታ እስከሚታይ ክሴ*
*ክፉ ደግ አልልም ዝምታ ነው መልሴ።*
*"…የሰው ልጅ ሆዱን ሲከፋው*
*ጊዜ እንደ ሰው ሲገፋው*
*መሄጃ መውጫ ሲጠፋው*
*ዝምታ ብቻ ነው ተስፋው።*

❋ ❋ ❋







Scanned with CamScanner







ከሲጄ ሩታ ኦርኪያ ጋር

Scanned with CamScanner







Scanned with CamScanner











Scanned with CamScanner









Scanned with CamScanner









Scanned with CamScanner



ንግድ

# «በማስታወቂያ አያመንኩ፣ በቴሌቪዥን ማስታወቂያ ተጠቃሚ ልሆን አልቻልኩም»

## ወ/ሮ አስቴር ሠይፌ

Scanned with CamScanner

# ክፍል አስራ ሦስት

## ሁሉዬ

*"ለኑሮዬ ማማር ስለፋ ስደክም*
*ነገር የወጋውን ቁስሌን እንዴት ላክም?*
*...ሽመል ጉራዴውን ስንቱን ጦር መክቶ*
*እንዴት ይኖራል ሰው በነገር ተወግቶ?"*
*ከአርቲስት ማሕሙድ አሕመድ ዜማ የተወሰደ*

- 1 -

ስንብት እንዴት ነው? ጠዋት ከእንቅልፏ ነቅታ ለሰላምታ እንደምትፍለቀለቀው ጮራ በሳቅ ተጠምቄ ልሰናበታቸው? ወይስ እድሜና ውበቷ እንደመሸባት እንደ ማታዋ ጀምበር፣ አንገቴን ደፍቼ "በሉ ደህና ሁኑ" ልበል? እንዴት ነው ስንብት?

የማደርገው ቢጠፋኝ ደብዳቤ ጽፌ እመሳቢያው ውስጥ አኖርኩ። ንብረቶቼ - ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀሱ ሃብቶቼን በሙሉ አበብዬ ለተባለ ወዳጄ ውክልና ሰጠሁ። የቤቴንና የድርጅቶቼን ንብረቶች እንድታስተዳድር ደግሞ ሁሉዬን ወከልኩ።

ብዙዎቹ የቤት ሰዎች በሶስት አሊያም በአራት ቀናት ተመልሰን እንደምንመጣ አምነዋል። እኛም ብንሆን ከዚህ የተለየ ግምት አልነበረንም። ለዚህም ይመስለኛል ማንንም ሳንሰናበት ከአገር የወጣነው። በተለይ የሁሉዬ እና የንግስት ነገር እንስፍስፍ አድርጎ ሊገድለኝ ነበር። ገና ሳልሄድ ናፈቁኝ። ገና ሳልለያቸው ፍቅራቸው ራበኝ፤ ጠማኝ። በተለይ የንግስት ሁኔታ ስላላማረኝ እውነቱን ብነግራት ትረበሻለች ብዬ አልተሰናበትኳትም። በልቤ አደራውን ለሁሉዬ ሰጥቼ እንደ ሌባ ሹልክ ብዬ ከአገር ወጣሁ።

ለነገሩማ የተገፋ ሰው ምን ብሎ ይሰናበታል? መሄጃዬን የማላውቅ ሴትዮ፣ ወዴት ልሄድ ነው ብዬ ልሰናበት? ምን ቋንቋ ይኖረኛል? ምንስ ብል ያምርብኛል? እግዜር የጣለኝ ሴትዮ፣ እግዜር ይከተልሽ ሊሉኝ ነው? አድባር የተፋችኝን ሴትዮ፣ አድባር ትሁንሽ ብለው ሊመርቁኝ ነው? አገሬ





የወረወረችኝን ሴትዮ፣ የምትደርሽበት አገር እጅን ዘርግቶ ይቀበልሽ ብለው ሊመኙልኝ ነው?

አውሮኘላን ላይ ወጥቼ ቁልቁል የአገሬን ምድር ሳየው የተሰማኝን መሪር ሃዘን በየትኛውም ቃል ልገልፀው አይቻለኝም። አውሮኘላኑ ከፍ ከፍ እያለ ሲሄድ፣ በመስኮት አሻግሬ ያየሁት የአገሬ ሰማይ ከመቼውም የበለጠ ልዩ ትርጉም ሰጠኝ። ይሄኔ ሆዴም፣ ልቤም፣ አንጀቴም፣ ዓይኖቼም አለቀሱ። የልጄን ጭንቅላት አንገቴ ስር ቀብሬ እዬዬ አልሁ።

አገር እያልኩ የኖርኩት ማንን ነው? አገሬ ማነው? አገሬ ጋሻዬ ስል የዘመርኩት ለማን ነው? አገሬ ዋስ ጠበቃዬ ስል ያቀነቀንኩት ለማን ነው? ለሜዳ ተራራው ይሆን እንዴ? ለወንዝ ሸለቆው ወይስ ለነፋስ ዝናቡ? ወይስ ለምድር ሰማዩ? ታዲያ ምነው ሜዳውን አቋርጬ፣ ተራራውን ወጥቼ፣ ወንዙን ተሻግሬ፣ ሸለቆውን አልፌ ስሄድ አገሬ ዝም አለኝ? ታዲያ ምነው ንፋሱ ወደ ባዕድ አገር ገፋኝ? ምነው? ምነው ምድሪቱስ እሪሪ አላለች? ሰማዩስ ጠበቃ አልሆነኝ? እረ አገሬ ማነው ሰዎች? ወገኖቼ ጠፉብኝ። ፍትህ ዘነጋኝ። አገር ከመዝገቡ ፍቆ አወጣኝ። ወዲህ ባይ፣ ወዲያ ባይ ሁሉም ጨለማ ሆነብኝ። የሰው ያለህ ብዬ ብጣራ፣ ጩኸቴን አሞራ በላው። የእውነት ያለህ ብዬ በምሬት ባነባ፣ እንባዬ ተመልካች አጣ።

ያኔ መፍጨርጨሬ ዋጋ እንደሌለው ስረዳ፣ እንዲያውም ለማላውቃቸው ጠላቶቼ ደስታቸውን ከማወፈር ያለፈ እርባና እንደሌለው ስገነዘብ፣ ያዙኝ ልቀቁኝም ሆነ እሪታዬን ዋጥ አድርጌ፣ እንደ ግንባሬ የኮሰተረውን አንጀቴን እያባበልኩ ጉዞዬን ጀመርኩ። ቢያንስ ሞት ከፊቴ መኖሩን ሳውቅ መጠነኛ እፎይታ ተሰማኝ። ሞቴን ማን ሊወስድብኝ ይችላል? አይ የመድኃኒዓለም ጥበብ - ለካ ሞትም ተስፋ ነው!

- 2 -

ኬንያ ስንደርስ፣ የአፍሪካ ቫኬሽን ክለብ አባል በመሆኔ የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ተደረገልን። ዕቃችንን ተቀብለው ሆቴል አደረሱልን። ነገር ግን የሆቴሉ ክፍያ ውድ ስለነበር፣ ከአንድ ሳምንት በላይ ለመቆየት አልቻልንም። ወዲያው ወደሌላ ሆቴል ተዛወርን።

ገንዘባችን እየተመናመነ ሲሄድ ሶስታችንም ተረበሽን። በዚህ ጊዜ ነበር ልጄ፣ ሁኔታውን ኬንያ ላይ ለተቀመጠው የኢትዮጲያ ኤምባሲ ማሳወቅ እንዳለብን ሃሳብ ያቀረበችው። እኔም ባለቤቴም ሃሳቧን ወደድነው። ወደ ኤምባሲው ጽ/ቤት ሄደንም ቀጠሮ አስይዘን ተመለስን።

በቀጠሮው ቀን ወደ ጽ/ቤቱ ኃላፊ ዘንድ ቀርበን የደረሰብንንና አሁን ያለንበትን ሁኔታ በድጋሚ ገለፅን። ኃላፊው የእኛን አቤቱታ በጥሞና ካዳመጡ በኋላ "አድራሻችሁን ጠይቀን አግኝተናል። ፖሊስ ጉዳዩን



Scanned with CamScanner

እንደያዘውም ተረድተናል። በዚያ ላይ ጉዳዩ እናንተ የምትሉትን ያህል አስጊ አይደለም። ወደ ኢትዮጵያ ሄዳችሁ ጉዳያችሁን ብትከታተሉ የተሻለ ይመስለኛል። ምክንያቱም ጉዳዩ ከግለሰቦች ጋር የተያያዘ ነው" በማለት አለሳልሰው መከሩን።

አዋቂ የማያውቁትን ቢነግርዎ ምን ይላሉ? እኛንም የገጠመን ይህ አይነቱ ነው። ወደ ኢትዮጵያ መመለሱማ መች ጠፋን!

ለኤምባሲው ሃላፊ የንግስትን ልጆችም "እባክዎን ላምጣቸው ይፍቀዱልኝ" ብያቸው ነበር። ህጻናቱ ቪዛ ማስመታት የሚችሉት እዚያው አዲስ አበባ እንጂ እዚህ አይደለም አሉኝ።

ወደ አዲስ አበባ ስደውል ቤቶቼ ለፖሊስ፣ ለወረዳ፣ ለፌዴራል.. እንዳመለከቱና ምንም ውጤት እንዳላገኙ ነገሩኝ። ቆይቶ ደግሞ ጉዳዩ እስከ ማዕከላዊ መድረሱን፣ የተከሰው ሰውዬም ተይዞ ፍርድ ቤት መቅረቡንና በዋስ መለቀቁን ገለፁልኝ።

በሶስት ወይም በአራት ቀን ውስጥ እውነቱ ወጥቶ ወደ አገሬ ለመመለስ የነበረኝ ተስፋ ጨለመ። እውነቱ ከመውጣቱ ይልቅ ይበልጥ እየተወሳሰበ ሄደ። ኤምባሲውም ወደ ኢትዮጵያ መመለስ እንዳለብን ነግሮናል። ይባስ ብሎ በጥገኝነት ያለንበት አገር መንግሥት ባፋጣኝ እንድንወጣ አስጠንቅቆናል። "ከድጡ ወደ ማጡ" ማለት ይህ ነው።

ይህንኑ ወደ አዲስ አበባ ደውዬ ለሁሉዬ ስነግራት "በፍፁም እንዳትመለሽ! ኢሕአዴግ ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ መግባት አትችይም!" አለችኝ።

"እንዴት?"

"ጄኔራል ምንትስ የተባለ አንድ የኢሕአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣን በጉዳዩ ላይ እጁ አለበት ተብሏል!" ብላ ጣሳታችሁ ይደንግጥ ክው አደረገችኝ።

እዚህም ያለው ነገር ተመሳሳይ ነው። ምንም ዓይነት ተስፋ አልታይሽ አለኝ።

አሁን ያለን ተስፋ ህይወት ራሷ የምትሰጠንን በረከት ወይም መርገም መጠበቅ ብቻ ነው። ነገር ግን ገንዘባችን እየተመናመነ በመሄዱ ኑሮውን መቋቋም አልቻልንም። ስለዚህ አገር እንቀይር ብለን ወሰንና የመስቀል ዕለት መስከረም 17 ቀን 1998ዓ.ም. ደቡብ አፍሪካ ገባን።

ደቡብ አፍሪካ የተቀመጥነው እክስቴ መብራቴ ጋ ነው። እርግጥ ቤቶቼ ከአዲስ አበባ ቡና ቤቶቼ የሰሩትን ሰቃቅመው አንስተው ይልኩልናል። ግን ምንዛሬው ዋጋ እጥቶ ሲበቃን አልቻለም። እነ መብራቴም እኛን ለማስተናገድ አቅማቸው አይፈቅድም። ስለዚህ አንድ የሆነ ሱቅ ከፍተን ለመስራት አሰብንና ከስንት መጉላላት በኋላ አደረግነው።

ሥራው ግን እንደጠበቅነው ቀላል አልሆነም። ለሰዉም ለአገሩም ባዳ ነን። በዚያ ላይ የቤት ኪራዩም ቶሎ ቶሎ ይደርሳል። ሥራው ትርፍ





የለውም። ከአዲስ አበባ የሚላከው ገንዘብ እንኳ ለሱቁ ማንቀሳቀሻ ነበር የሚውለው።

ሱቁ ያልሰሩበት፣ ያልለመዱት አገር ሆነና ውጤት አጣ። በዚያ ላይ በየጊዜው በሌቦች ይሰበራል። አስቸጋሪ አገር ነው። በኋላ እሱን ትተን የሃበሻ ምግብ ቤት ከፈትን። በአካባቢው ያለው አንድ የሃበሻ ምግብ ቤት ብቻ በመሆኑ ቶሎ ለመደልን። ጥሩ እየተንቀሳቀስን ሳለ "መኪና ማቆሚያ አጣን፣" በሚል ምቀኝነት አስዘጉን። ሌላ ቦታ፣ ሌላ ቤት ተከራይተን መስራት እንደጀመርን ደግሞ "የውጪ አገር ዜጋ በምግብ ቤት ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም" በሚል ሰንካላ ምክንያት ችግር እየፈጠሩ ሲያስቸግሩን ያንንም ቤት ለመልቀቅ ተገደድን።

እናም ነገሮች ከበዱኝ። ችግር ከምንጊዜውም ገዝፎ እላዬ ላይ ተከመረ። ድሮውንም አልቃሻ ነኝ፣ ኑሮዬ መስመር አልይዝ ሲለኝ እዬዬዬን አስነካሁት። የተጠራቀመ ብሶቴን በሰበቡ አወጣሁት።

አንድ ቀን፣ አቶ ከበደ የሚባሉ፣ ከእናቴ ወገን የሆኑ ሰው ለሁሉዬ ደውለው፣ እዚህ ለምን እንደመጣሁና አሁን በምን ዓይነት ይዞታ ላይ እንዳለሁ ጠይቀው ተረዱና በሁኔታዬ አዝነው እዚህ ላለው ልጃቸው ደወሉለት።

"አንቺ ብቻ በርቺ፣ አንድ መላ እናጣም" ማለታቸውንም ሰማሁ። በእውነቱ ደስ አለኝ። ችግሬን ሰምቶ የሚያዝንልኝ ሰው በማግኘቴ እጅግ ደስ አለኝ። የሚቆረቆርልኝ፣ ሊረዳኝ የሚፈልግ ሰው በማግኘቴ ደስ አለኝ። ከወዲያ ከወዲህ በዘመድ አዝማድ በመጠጋገኔ እንደማልወድቅ ተሰማኝ።

* * *

ከጥቂት ቀናት በኋላ የአቶ ከበደ ልጅ፣ ዘሪሁን ሊጠይቀኝ መጣ። "አባቴ ትንሽ ብር ልኮልሻል። አይዞሽ በላትም ብሎኛል" አለና የተጠቀለለውን ዳጐስ ያለ ብር ሰጠኝ። ቆጠርኩት። ማመን ተሳነኝ። ልጃቸውን፣ ዘሪሁንን ያየሁት ልጅ እያለሁ ነበር። ለእሱም ሆነ ለቤተሰቡ ያደረግኩላቸው አንድም ነገር የለም። ያስተማርኳቸውና ለቁም ነገር ያበቃሁዋቸው ብዙ ልጆች አሉ። ነገር ግን አንዳቸውም ዞረው አላዩኝም። አንዳቸውም ተመልሰው የቤቴን በር አላንኳኩም። ዘሪሁን ግን ጥቂት እንኳ ሳላደርግለት ከዚያች ቀን ጀምሮ ብዙ ውለታ ዋለልኝ።

መልሼ እጀ ላይ የተከመረውን ጥቅል ብር አየሁት። መልሼ ቆጠርኩት - ሃምሳ ሺህ ብር! ኦ አምላኬ!

የእክስቴ መብራቴ ባለቤት ደግሞ መቶ ሺህ ብር ሰጠኝ። ከራሴና ከሌሎች ሰዎች ካገኘሁት ጋር ተደምሮ ገንዘቡ ወደ አራት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር አደገ። ቤት ልገዛ አሰብኩ፣ ለዚያ ግን የዜግነት መታወቂያ ማውጣት አለብኝ። የዜግነት መታወቂያውን ያለ ብዙ ውጣ ውረድ አገኘሁ። ወዲያው ቤት ገዛሁ። ቤቴን በሂደት ወደ ንግድ ማዕከልነት ለወጥኩት። ሲጀመር



Scanned with CamScanner

ጆሮዬን ይሁን ደዋዬን ማመን ቸገረኝ። ብቻ አንዱ ልክ አይደለም። ወይ ደዋዬ ጋ ወይ ጆሮዬ ጋ ችግር አለ። በእርግጥ የቤቴ ነገር ብዙ ጣጣ እንዳለው ልቤ ሹክ ይለኝ ነበር። ይህን ያህል ገፍቶ፣ እኔንም በረሃ ላይ አውጥቶ ይጥለኛል ብዬ ግን ለቅጽበትም ቢሆን አስቤው አላውቅም።

"ለመሆኑ ይህን ሁሉ የሚሰራው የቤቴ ሰው ነው?"

"እስት፣ እስኪ ዛሬ እንኳ ጠርጥሪ።"

"ለምን አፌን አበላሻለሁ? በዚያ ላይ የምጥረጥረው ሰው ቢኖር ኖሮ እስከዛሬ ለምን ብዬ እቆያለሁ። ለመሆኑ ይህን ጉዴን ሁሉዬ አውቃለች?"

ደዋዬ ሳቁን መቆጣጠር ተሳነው። ግር አለኝ። ወዲያው እንደ መደንገጥ ብሎ "እስት፣ ጠላትሽኮ..." አላስጨረስኩትም።

"ማነው? ንገረኝ!"

"ሁ-ሉ-ዬ! ሁሉዬ ራሷ ናት፣ እስት።"

## - 3 -

"ተፈጥሮ የመከራ ደሃ አይደለችም" ያለው ሰው ምን ያህል መከራ ቢበዛበት ይሆን?

ሩታ እንደነገረችኝ፣ እህቴ ንግስት ለሁለተኛ ጊዜ ተመርምራ በሽታው እንዳለባት ተነገራት። እነ ሁሉዬም በየቤተክርስቲያኑ እየወሰዱ፣ እራቁቷን እያቆሙ ምስክርነት ስጪ እያሉ እንደሚያስገድዷት፣ በስምሽ ቤተክርስቲያን ይሰየማል እያሉ እንደሚያሾፉባት ሰማሁ።

ልጅ ይህን ሁሉ የምትነግረኝ የንግስት ህይወት ካለፈ በኋላ ነው። ለሰባት ዓመት ከኤች አይ ቪ ቫይረስ ጋ በሰላም የኖረችው እህቴ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ከሰውነት ተርታ ወጥታ፣ እጅግ በሚዘገንን አኳኋን ተሰቃይታ እንደሞተች ከሩታ ፊት ላይ ተረድቼያለሁ። "ራቁቴን አቁመው ምስክርነት ስጪ ሲሉኝ፣ ካሁን በኋላ ወደ ቤተክርስቲያን አልሄድም ብያቸዋለሁ" ብላ በነገረቻት ነገር ውስጥ ብዙ የሚያሳዝን፣ ብዙ ተስፋ የሚያቆርጥ፣ ብዙ ህይወትን የሚያስጠላ ነገር መኖሩ ታወቀኝ። እኔ ለሰባት ዓመት ቫይረሱ እንዳለባት ሳታውቅ እንድትኖር ባደርግም፣ ሁሉዬ ግን ምስጢራችንን ገልጣ እህቴን አሳቅቃ፣ አይሆኑ ሆና እንድትሞት ፈረደችባት። ለእህቴ አነባሁ። ለመሞቷ ብቻ ሳይሆን እስክትሞት ድረስ ላየችው መከራ አምርሬ አለቀስኩ።

ቆየት ብሎ ደግሞ ሁሉዬና ግብረ አበሮቿ ቤቴን ጥለው መውጣታቸውን፣ የቤቴን ዕቃዎች መሰባበራቸውን፣ ወርቅና ገንዘቤን መውሰዳቸውን፣ በኔ ገንዘብ ይሁን አይሁን እስካሁን ባላረጋግጥም የራሳቸውን ቡና ቤት መክፈታቸውን፣ የኔን ሠራተኞች በማባበልም





በማስገደድም ወደራሳቸው ማዛወራቸውን ሁሉ ሰማሁ። ሌላው ቀርቶ "ደመወዝ አልከፈለችንም" ብለው ለክስ መዘጋጀታቸውን አወቅሁ።

የእህቴ ገዳይ፣ የልጁ አሳዳጅ፣ የእኔ ሰላይ፣ የባለቤቴ አስደብዳቢ፣ ሁሉዬ ናት ብዬ ልመን? ከሞቀው ቤታችን ጠርጋ ጭው ባለ በረሃ ላይ የጣለችን፣ ሁሉዬ ናት ብዬ ልመን?

ቤቴን ያመሳቀለችው፣ ህይወቴን የመረዘችው፣ ኢትዮጲያዊነቴን ለመስረዝ የሞከረችው ያቺ የቀድሞዋ አሳቢዬ፣ ያቺ የቀድሞዋ ተቆርቋሪዬ፣ ያቺ የቀድሞዋ ተንከባካቢዬ ሁሉዬ ናት ብዬ ልመን? በየሄድኩበት እንደ ጥላ እየተከተለች የምታስፈራራኝ፣ ውጥኔን ሁሉ በማበላሸት ተስፋዬን የምታቀዘቅዝብኝ፣ "ለዚህ ሁሉ የዳረጉሽ አባትሽ ናቸው" ብላ የደለለችኝ፣ "ወደ ውጭ አገር ሄደሽ እረፍት አድርጊ" ብላ የተጫወተችብኝ፣ "ኢሕአዴግ ከመውደቁ በፊት አገርሽ እንዳትመለሺ" ብላ በኔዋ የፖለቲካ መሃይም ላይ ሽብር የለቀቀችብኝ... ያቺ የጠላቶቼ ሁሉ መነሻ፣ ያቺ የውድቅቴ ሁሉ ውጥን፣ ያቺ የኪሳራዬ ሁሉ መሠረት፣ ያቺ የህመሜ ሁሉ ጦስ... የኔዋ ሁሉዬ ናት ብዬ ልመን? ያቺ "እስት" ብላ የምታቆላምጠኝ ሰው ጠላቴ ናት ብዬ ልመን?- - -

ደከመኝ። መንፈሴን ደከመኝ። ምኞቴን ደከመኝ። ተስፋዬን ደከመኝ። እምነቴን ደከመኝ... አ! አምላኬ!

መቸም ቢሆን አጣቸዋለሁ ብዬ የማልወራረድባቸውን ሶስት ሰዎች ባንዴ አጣሁ። ሶስቱም ጌጦቼ ነበሩ። ሶስቱም የደስታዬ ምንጮች ነበሩ። እነሱን ሳይ ዓይኖቼ ይበራሉ። አፌ በሳቅ ይሞላል፣ መንፈሴም በእልልታ ይዘምራል።

ሩታን የማያት እንደ ልጅም እንደ ጓደኛዬም ነው። አምናታለሁ፣ እመካባታለሁ። ይህ እምነቴ ግን የቆየው ለጥቂት ጊዜያት ብቻ ነው። በሰው አገር ኑሮን ለማሸነፍ ደፋ ቀና በምንልበት ባንዱ ቀን፣ አንድ ወጣት ከአዲስ አበባ እኛ ጋ መጣ። ቀጠሮ አልነበረንም። ሌላው ቢቀር እውቅና እንኳ የለንም። ከእኛ መሃል ወጣቱን የምታውቀው ሩታ ብቻ ነበረች።

ከአገር ከወጣን ጀምሮ የሩታ ባህርይ ተቀይሯል። ዝምታ ታበዛለች። ትነጫነጫለች። ሆድ ይብሳታል። እንዲህ ስታስብና ስትጨነቅ የቤተሰብ ናፍቆት ስለሚመስለኝ ምን ሆነሽ ነው? ብዬ የበለጠ ላበሳጫት አልፈለግሁም። ዛሬ ግን ያ ሁሉ ሃሳብና ጭንቀቷ ከላይዋ ላይ ተገፎአል።

"ሰውን ማመን ቀብሮ ነው" አለች ቀበሮ! ለካስ ያ ሁሉ ጭንቀቷ ለዚህ ወጣት ኖሯል! ልጁ እሷን ለማግኘት ለቤተሰቦቹ ነግሮ ነው የመጣው። ጓደኛ ይኖራታል ብዬ ለአንዲት ደቂቃ እንኳ አስቤ አላውቅም። እንዲህ ታደርጋለች ብዬ በፍፁም አልጠበኩም ነበር። ለሰው ደግ ስውል፣ ደግነቱ በልጁ ላይ ይውላል እያልኩ ነበር። መልካም ሳደርግ፣ መልካምነቱ ለልጄም ይተርፋል በሚል ተስፋ ነበር።



Scanned with CamScanner

አንድ ትቼው የማልሄድ ጉዳይ ያለኝ መስሎ ይሰማኛል። አንድ የምጓጓለትና የምኖርለት ነገር አለኝ።

❋ ❋ ❋

አሁን አሁን ስለ ሁሉዬ የሚሰማኝን ስሜት በትክክል አላውቀውም። አንዳንዴ ብስጭቴ ይብስና፣ በየትኛውም መንገድ እጇን ለፍርድ ማቅረብ እንዳለብኝ ይሰማኛል። ሌላ ጊዜ፣ መድኃኔዓለም የእጇን ይስጣት እልና እጅንና እግሬን አጥፌ እቀመጣለሁ። ይህ እንደማይሆን ግን እርግጠኛ ነኝ። የመድኃኔዓለም ፍርድ በሰማይ ነው። የሰማዩም ጌታ በሰማዩ ህግ ይዳኛት። እኔ ግን ምድራዊ ነኝና በመሬት ህግ እፋለማታለሁ። ከቤት አውጥታ ስለጣለቻቸው ተማሪዎች ስል በህግ እፋለማታለሁ። እንደ አሮጌ ቁና የትም አውጥታ በወረወረቻቸው አካል ጉዳተኛ ሰዎቼ ስል በህግ እፋልማታለሁ። ለሩታ ህይወት ስል እፋለማታለሁ። ዛሬም ቢሆን ቤቱን መጠለያቸው ላደረጉ፣ ከሰላሳ ለሚበልጡት ሰዎች ስል አቤት ማለቴን አላቆምም።

ዛሬም ብዙ ሰዎች እየደወሉ ይጠይቁኛል። ያፅናኑኛል። ያበረታቱኛል። "መንግሥት'ኮ ያለበት አገር ነው" እያሉ የጥሪ ድምፄን እንዳሰማ ይጐተጉቱኛል።

አንዳንድ ዘመዶቼና ወዳጆቼ "አይዞሽ፣ እውነትና ንጋት ገሃድ መውጣቱ አይቀርም" እያሉ ያበረታቱኛል። እውነቱን ማን እንደሚገልፀው ባላውቅም፣ ቢያንስ ተቆርቋሪ ወገን እንዳለኝ ማወቁ በራሱ ተስፋ ነው።

እዚህ ደቡብ አፍሪካ የምኖረውን ኑሮ ለመግለፅ ያዳግተኛል። እንደ ገደል ዳር ቁጤማ በተነነው በበነነው እየሰጋሁ፣ ሞቴን ተስፋ አድርጌ ነው የምኖረው። ከፊቴ ያለው ነገር ሁሉ ያስፈራኛል። ከኋላዬ ያለው ዓለም ያስበረግገኛል። በመስታወት ውስጥ የማየው የራሴው ምስል ያሸብረኛል። ዓለሙ ሁሉ ሥጋቴ ነው። ማን ወዳጄ፣ ማንስ ጠላቴ መሆኑን ስለማላውቅ፣ ተስፋዬን በማን ላይ መጣል እንዳለብኝ አላውቅም። አዲስ አበባ ባሉ ወኪሎቼ ላይ? ጉዳዬን በያዘው ፖሊስ ላይ? በማያውቀኝ፣ ግን ፍትህ ወዳድ በሆነው በወገኔ ላይ? ወይስ በእግዜር ላይ? እንጃ።

እንባቢዎቼ ሆይ፣ ደሜ እንደ እናንተው ጠይም ነው። አካሌም መንፈሴም የእናንተው ክፋይ ነው። የነፍሴ ስስት ይገባችኋል። የመንፈሴ ባይተዋርነት ይሰማችኋል። የህይወቴ ድቀት ይከስትላችኋል። የተስፋዬ ስብራት ይገለጥላችኋል።

ዛሬ አገር የለኝም። ዛሬ ሰው የለኝም። ዛሬ ማንም ምንም አጠገቤ የለም። ከሥራ የማይለየው እጄ እንኳ ሆዴን አቅፎ እሹሩሩ ሲል ነው የሚውለው። ዓይኖቼ ነገን በተስፋ ማየት አቁመው፣ ትላንትም እየከለሱ በእንባ ይጫወታሉ።





ዛሬ የተስፋ እስረኛ ነኝ። የነፃነት ደሃ ነኝ። ሰው እፈልጋለሁ። ወገን እፈልጋለሁ። አገር እፈልጋለሁ። እባካችሁ፣ ፍትህ ዘግይቶብኛልና፣ አገሬ ናፍቆኛልና አግዙኝ። የምታውቁኝ በምታውቁት መንገድ ለአገሬ አብቁኝ። የማታውቁኝም ፀልዩልኝ። እንደ አሮጌ ቁና የትም ተጥያለሁና ሁላችሁም አለሁሽ በሉኝ።

አገሬ ጠበቃዬ ትሆን ዘንድ እመኛለሁ። መንግሥትም የእንባዬ ጠራጊ ይሆናል ብዬ አምናለሁ። ያኔ ልቤ ከሞት ይነሳል። የምምገውም አየር ሰላምና ተስፋ የሞላበት ይሆናል።

ያኔ አገር አለኝ፤ ወገን አለኝ እላለሁ።

## - ተፈፀመ -



Scanned with CamScanner

የባለታሪካችን አስቴር ሠይፌ ቤተሰብና ወዳጅ የሆነችው ወጣቷ ድምጻዊት *ማርታ ጌታቸው* በተቀነባበረ የሐሰት ወሬ የአስቴርን አገር ጥሎ መሰደድና በሰው አገር መቸገር አንገብግቧት በአገር ባህል ዜማ ቅንብር እንዲህ ስትል በመረዋ ድምጿ አቀንቅናላታለች። ድምጻዊቷ ዜማው በቅርቡ ለህዝብ ጆሮ እንደሚደርስ አጫውታናለች። እስከዚያው የዜማው ግጥም እንደሚከተለው አቅርበነዋል፦

*አለመታደል ነው ወይንስ ምን ይሆን?*
*ሰምሽን ያደረጉት እንዳይሆን እንዳይሆን*
*ተገኝተሽ አይደለም በከፋት ጉዳና*
*ውለታሽን ሁሉ ያደረጉት መና።*
*ልብሽ ቢያዝን ቢከፋ*
*አይዞሽ ባይ ከጉንሽ ቢጠፋ*
*ተሰደሻል ከሰው አገር*
*አላኖር ስላለሽ የሰው ነገር*
*ለሰው ልጅ አዛኝ ለከፋው ደራሽ*
*ሆነሽ እያለ አልባሽ አጉራሽ*
*ነገሩ ሆነ ተገላቢጦሽ*
*ሰምሽን አጉዳፊ ከከፋ ጥሎሽ*
*ወሬ ተወራ ተቀነባብሮ*
*አንቺን ዳረገሽ ለስደት ኑሮ*
*በጣም ይገርማል የሰው ተፈጥሮ*
*ምን ይጠቀማል በሰው አሲሮ?*
*እንዲህ አልነበረም የሰው ብድሩ*
*እስከሚሰደድ ከውድ አገሩ*
*መሆን ቢገባው ውለታ መላሽ*
*የጎረሰውን ሆነ እጅ ነካሽ*
*እንዳያልፍ የለ ሁሉም አለፈ*
*ወሬ ወሬ ነው ምን አተረፈ?*
*ለጊዜውም ቢሆን ምንም ፈተና*
*መምጣትሽ አይቀር ጊዜ አለ ገና!*





አስተያየት ልትሰጡኝ፣ ልትረዱኝ ስምትፈልጉ ·


ኤ-ሜይል አድራሻ፦
rationeday@yahoo.com

ፖስታ አድራሻ፦
RUTA ARAYA
NO 9 PERKIN STREET
NORTH END
PORT ELZABETH
SOUTH AFRICA

ወይም
ASTER SEIFE
c/o KASSAYE TEKESTE
P.O.BOX 70491
ADDIS ABABA
ETHIOPIA




Scanned with CamScanner

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

EMAY Printers